# በተመረጡ የአቦነህ አሻግሬ እንቁጤ እቁጣጣሽ እና ሌሎች ልቦለዶች ውስጥ የቋንቋ አጠቃቀምና የይዘት ትንተና

በ

ይኸነው የኔነህ

ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል
ለአረት ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ሰኔ 21/10/001 ዓ.ም

# በተመረጡ የአቦነህ አሻግሬ እንቁጤ እቁጣጣሽ እና ሌሎች ልቦለዶች ውስጥ የቋንቋ አጠቃቀምና የይዘት ትንተና

በ

ይኸነው የኔነህ

ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል
ለአረት ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

የጥናቱ አማካሪ
አየለ ፍቅሬ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ሰኔ 21/10/001 ዓ.ም

# ምስጋና

- ሁሉ ነገር በጁ የሆነው አምላክ ቸሩ እግዜአብሔር ለዚህ ስላበቃኝ ምስጋናዬ ወደር የለውም፡፡
- በሁሉ ነገር ድጋፍ በመስጠት፣ የአባትና የእናት ፍቅራችሁን በመለገስ ከዚህ ላደረሰችሁኝ ወላጆቸ አቶ የኔነህ ኃይሉና ስንታየሁ አባዋ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡
- ለኔ ብለው እጃቸውን ያረባረቡ ዘመዶቼ፣ ጓደኞቼ፣ ምስጋናየ የላቀ ነው ውለታም መላሽ ያደርገኝ፡፡
- ሥህተቴን በማረም፣ ቀናህ መንገድ በማመለላከት፣ የምናል ድጋፍ በማድረግ ጽሁፌ መልክ እንዲኖረው ላደረገኝ አማካሪ አቶ አየለ ፍቀየ ምስጋናየ የላቀ ነው፡፡
- በብዙ እንቅፋቶችና መሰናክሎች ላልተሸነፉሁትና ላልተበገርሁት፣ ሊጨርሰኝ ሲል የጨረሱት እኔነቴንም እንዲሁ አመሰግናለሁ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ይዘትና የቋንቋ አጠቃቀም በአቦነህ አሻግሬ እንቁጤ-እንቁጣጣሽና ሌሎች ልቦለዶች ውስጥ የተሰኘው የዲሪ ማሟያ ጽሁፍ አራት ምዕራፎች አከቷል፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱ ዳራ፣ ዓላማ፣ ወሰን፣ጠቀሜታ አን የአጠናን ዘዴ አካቶ ይዟል፡፡ ሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ በንድፈ ሀሳባዊ መሰረት ስራ የይዘት ምንነት የቋንቋ አጠቃቀም ምንነትና እንዲሁም ከጥናቱ ገር ተዛማጅነት ያላቸውን ጥናታዊ ጽሁፎች ተገሰውበታል፡፡ የጥናቱ ሦስተኛው ምዕራፍ የጥናቱ ዋና አካል የቀረበበት ምዕራፍ ነው፡፡ በውስጥም የቋንቋ አጠቃቀም ትንተና አካቷል፡፡ የጥናቱ ቋንቋ አጠቃቀም ትንተና በተወሰኑ ምሁራን ሀሳብ የተጠናከረ ነው፡፡

ጥናቱ በምዕራፍ አራት ደግሞ የልቦለዶቹን ይዘት የተፈተሸበት ምዕራፍ ነው፡፡ ይዘቶቹ ወይም በምቦለዶቹ የተነሱ ፍሬ ነገሮች ማህበራዊ፣ ባህላዊ ነገሮችን የሚያሣዩ ናቸው፡፡ ይህም በዋና እና በንዑስ አላማቸው የተለዩ ናቸው፡፡ ከዚህ ስር ማጠቃለያ አብሮ የታየበት ገጽ ይገኛል፡፡

ጥናቱ የቋንቋ አጠቃቀምን ደግሞ በውስጡ እንግሊዘኛ፣ ቀበለና ቃላት የግዕዝ ቃላትን እንዲሁም ፈሊጣዊ ንግግርን ይዟል፡፡ እነዚህ የቋንቋ አጠቃቀም ከአጥኝው ሀሳብ በተጨማሪ የተወሰኑ ምሁራን ሀሳብ ወይም ብያኔ በሀሳቡ ማጠናከሪያ አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡

# ማውጫ

## አርእስት ገፅ

ምስጋና ....................................................................................................i
አጠቃሎ....................................................................................................ii
ማውጫ ....................................................................................................iii
ምዕራፍ አንድ
መግቢያ ....................................................................................................1
1.1 የጥናቱ ዳራ ....................................................................................1
1.2 የጥናቱ አላማ....................................................................................2
1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ................................................................................2
1.4 የጥናቱ ወሰን ....................................................................................2
1.5 የጥናቱ ዘዴ ......................................................................................2
1.6 የጥናቱ አደራጃጀት ............................................................................3
ምዕራፍ ሁለት
2. ክለሣ ደርሳን ....................................................................................4
2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት....................................................................4
2.2 ንድፈ ሀሳባዊ መሰረት .......................................................................7
2.2.1 የቋንቋ አጠቃቀም ምንነት በአጭር ልቦልድ .......................................7
2.2.2 የይዘት ምንነት ..............................................................................8
ምዕራፍ ሦስት
3. የቋንቋ አጠቃቀም በእንቁጤ እንቁጣጣሽ እና ሌሎች ልቦለዶች ውስጥ................10
3.1 የቃላት ምርጫ...................................................................................10
3.1.1 የግዕዝ ቃላት....................................................................................10
3.1.2 ፍካሬ ቃላት ......................................................................................12
3.1.3 ዘዬ ቃላት ........................................................................................14
3.1.4 የእንግሊዘኛ ቃላት..............................................................................16
3.2 የዘይቤ አጠቃቀም..................................................................................17
3.2.1 አነጻጸሪ ዘይቤ.....................................................................................17
3.2.2 ሰውኛ ዘይቤ.......................................................................................19
3.2.3 ተለዋጭ ዘይቤ ....................................................................................20
3.3 በቋንቋ አጠቃቀም የታዩ ድክመቶች ..........................................................21
3.3.1 የቃላት ድረታ ...................................................................................21
3.3.2 ጉራማይሌ ቋንቋ.................................................................................22
3.3.3 የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ አለመጣጣም ..........................................23
3.3.4 የአረፍት ነገር ቅንብር ጉድለት ...........................................................24
ምዕራፍ አራት
4. የልቦለዶቹ ይዘት ትንተና .....................................................................27
4.1 እንቁጤ እንቁጣጣሽ .............................................................................27
4.2 እልከኛው...............................................................................................30
4.3 ብሩ ከልቢሌ...........................................................................................32
ማጠቃለያ .................................................................................................35
ዋቢ መጽሐፍት

1. መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

በየዘመኑ ታትመው ለንባብ የሚበቁ አጫጭር ልቦለዶች አንባቢ ዘንድ ይደርሱ እንጅ የአዳዲስ ስራዎችን ጠንካራም ሆነ ደካማ ጎን የሚፈትሽ ከአስተያየት የዘለለ ጥናት ሲደረግ አይታይም ይባላል፡፡ እስካሁንም በጥናት ሳይዳሰሱ የቆዩ በርካታ ስራዎች እንዳሉ ይነገራል፡፡ ይህ መሆኑ ደራሲያን ወደ ፊት ስራዎቻቸውን አሻሽለው የሚቀርቡበትን ወይም አጠናክረው የሚገፋበትን አቅጣጫ እንዳይጠቆሙ ከማድረጉ በተጨማሪ ተደርሲያንም አጫጨር የልቦለድ ድርሰቶቹን ጥንካሬና ድክመት ለይተው እንዳያውቁ ያደርጋል፡፡

ይህ <u>እንቁጤ- እንቁጣጣሽ እና ሌሎች ልቦለዶች</u> የተሰኘው ልቦለድ በ2000 ዓ.ም ታትመው ከወጡት ተስዕሁፍ ስራዎች አንዱ በመሆኑና ደራሲው ምንም እንኳን ከዚህ በፊት ህጻናት ተውኔት <u>ኩኩ መለኮቴ</u>፣ <u>የሰማዩ ሰረገላ</u>፣ <u>አባጉጉ</u> ሦስቱንም በ1996 ዓ.ም. ሁለተኛ የአዋቂዎች ተውኔት <u>ሊቃማፅምር</u> (1999)፣ <u>ኩረባ</u> (1999) እና በሦስተኛም <u>ጥናታዊ የኢትዮጵያና ኢትዩጵያውያን በጥንታዊ ግሪክ እሳቤ</u> (1999) የሚሉ ሁለት ተውኔቶና አንድ ጥናታዊ ፅሁፍ አሉት በልቦለዱ ላይ ከዚህ በፊት ጥናት ባለመካሄዱ ልመርጠው ችያለሁ፡፡ ሌላው በርዕስ ጉዳዩ ጥናት ለማድረግ ያነሳሳኝ በተለይም በቋንቋ አጠቃቀም ላይ እንዳተኩር ያደርገኝ ቋንቋ እንደሌሎች ሁሉ ልቦለድን የማቅረቢያ ዋነኛ መሳሪያ በመሆኑ ደራሲንና ተደራሲን የሚያገናኝ ድልድይ ነው ብዬ ማመኔ ነው፡፡ ስለዚህም በሰነ ጽሁፍ ሠራዎች ላይ የሚደረግ ጥናት ምንጊዜም ከቋንቋ መጀመር እንዳለበት ይሰማኛል፡፡

በአጠቃላይ ልቦለድ ድረሰቱ ከተጻጻፈበት ጊዜ አንጻር የቅርብ ስራ ከመሆኑ ጋር ተያይዘው ለሚነሱ የልቦለድ የቋንቋ አጠቃቀም ምን ይመስላል? ደራሲው የተጠቀመበትን ቋንቋለማስተላለፍ የፈለገውን ይዘት በብቃት እንዲያስተላልፍ አስችሎታል ወይ?& የቋንቋ አጠቃቀሙ ምን ጠንካራና ደካማ ጎን አለው? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ የማግኘቱ ፍላጎት የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክኒያት ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዓላማ የደራሲውን ስነ ጽሁፋዊ ስልት በመመርኮዝ ልቦለዶቹን ከቋንቋ አጠቃቀም ማለትም ከቃላት መርጫ፣ ድግግሞሽ፣ የዓረፍት ነገር አወቃቀሮችና ዘይቤዎች አንጻር በመመርመር መተንተን ነው፡፡ በተጨማሪም ልቦለዶቹ የያዟቸውን ፍሬ ነገሮች በአብይ በንዑስ ጭብጣቸው መሰረት በመመርመር እየተነተኑ ማሳየት ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

ከዚህ በኋላ ሊኖር በሚችለው ሥነ ጽሁፋዊ ስራም ሆነ ስነ ጽሁፋዊ ስራዎች ላይ በሚደረግ ጥናት የዚህ ጥናት ውጤት ፋይዳ ይኖራል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህ ጥናቱ ወደፊት በዚህ ልቦለድ ላ ለሚደረጉ ጥናቶች እንደ መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላሉ ተብሎ ስለታሰበ፡፡

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

በዚህ ጥናቲዊ ጽሁፍ <u>እንቁጤ-ዕንቁጣጣሽ እና ሌሎች ልቦለዶች</u> በሚለው የአቦነህ አሻግሬ ድረሰት ውስጥ ሦስት አጫጭር ልቦለዶች በመምረጥ የቋንቋ አተቃቀምና የይዘት ትንተና ለማድረግ ነው፡፡ የደራሲውን የቃላት ምርጫ፣ የዘይቤ አጠቃቀም፣ የግዕዝ ቃላት፣ የእንግሊዘኛ ቃላት፣ የዓረፍተ ነገር አወቃቀሮች እና በቋንቋ አጠቃቀም ዙሪያ በደርሰቱ ውስጥ የተዬ ድክመቶች ፍተሻ ማድረግ ነው፡፡

## 1.5 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት መሰረት የሚያደርገው በቋንቋ አጠቃቀምና በይዘት ትንተና ውስጥ የሚነሱ ርዕስ ጉዳዮችን በማንሳት በልቦለዶቹ ውስጥ በምን መልኩ አገልግሎት ላይ እንደዋሉ በማየት ወይመ በመገምገም ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት በቋንቋ አተቃቀምና በይዘት ትንተና ዙሪያ የተሠጡ ንድፈ ሀሳቦችንና የተሰሩ መመረቂያ ፅሁፎችን /ዲማጾችንን/ በመመርኮዝ በገላጭ የምርምር ዘዴ ትንተና ለማድረግ ይታሰባል፡፡

## 1.6 የጥናቱ አደረጃጀት

የዚህ ጥናት አደረጃጀት የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ጥናቱ በአራት ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን በመጀረመሪያው ምዕራፍ የጥናቱ ደራ፣ አላማ፣ ጠቀሜታ፣ ወሰን፣ ዘዴና አደረጃጀት ይቀርቡበታል፡፡ በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትና ንድፈ ሀሳባዊ መሰረት ተፈትሸዋል፡፡ በምእራፍ ሶስት በቋንቋ አጠቃቀም ስር ባሉ ንኡስ ርዕሶች ተመስርቶ ትንተና ተደርጓል፡፡ በምዕራፍ አራት ሦስት አጫጭር ልቦለዶች በዐብይና በንዑስ ይዘታቸው ትንተና ተካሄዶ የጥናቱ ፍጻሜ ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2.ክለሳ ድርሰን

### 2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር ተዛምዶ ያላቸውን ስራዎች መመልከትና መፈተሽ ተገቢ በመሆኑ ይህን ጥናት ሳቀርብ ከጥናቱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ገኛሉ ብዬ የወሰድኳቸውን ሰራዎች አንብቢያለሁ፡፡ ይህን ጥናት ሳቀርብ የሰራ ትኩረቴ አድርጌ የተነሳሁበት ጉዳይ በአቦነህ አሻግሬ እንቁጤ-ዕንቁጣጣሽና ሌሎች ልቦለዶች የቋንቋ አጠቃቀምና የይዘት ትንተና በሚል በመድበሉ ውስጥ በወጡ አጫጭር ልቦለዶች ቋንቋቸውንና ይዘታቸው በመተንተን ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በቅኝቴ ወቅት በዋናነት ትኩረቴ አድርጌ የተመለከተኳቸው በአጭር ልቦለድ መድበል፣ በጋዜጣና በመጽሄት በወጡ አጫጭር ልቦለዶች ላይ የተሰሩ ጥናቶችን ነው፡፡ እነዚህ በአጭር ልቦለድ ዙሪያ የተሰሩት ቁጥራቸው ወደሰ ሀያ ዘጠኝ /29/ ይደርሳሉ፡፡ እኔ ግን ለጥናቱ የቀረቡትን ሰባቱን ብቻ ለማየት ምክሪያለሁ፡፡ በዚህ መሰረት መርጨ የቃኘኋቸው ጥናቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

የሻረግ ምትኩ /1979/፡- “በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የወጡ አጫጭር ልቦለዶችን መገምገም” በሚል የተሰራ ነው፡፡ የሻረግ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የወጡ አጫጭር ልቦለዶችን አንጻር ታሪክና መቼት ስትገመግም በተመሳሳ መልኩ ልበለዱን ስትገመግም ደራሲው የተጠቀማቸውን ቋንቋዎች ዳሰሳ አድርጋለች፡፡ እኔ ደግሞ የአቦነህን ድርሰት ከቋንቋ አጠቃቀምና ከይዘት አንጻር መተንተን ነው፡፡ በዚህም በልቦለዶቹ ውስጥ ያሉትን ፍሬ ነገሮች እና ደራሲው ምን አይነት ቃላትን እንደተጠቀመ ገምግሚለሁ፡፡ ልነታችን የሻረግ አንጻር፣ ታሪክና መቼት በመገምገም እኔ ደግሞ የእያንዳንዱን አጭር ልቦለድ ፍሬ ነገር በመተንተን እና የቋንቋ አጠቃቀምን በስፋት በመዳሰሴ፡፡ የምንመሳሰለው በአጭር ልቦለድ ዙሪያ ሰርተን የደራሲዎችን የቋንቋ አጠቃቀም ድክመቶች መዳሰስና የአጭር ልቦለድ ቃላት ምን ይመስላሉ የሚሉትን ማየታችን ነው፡፡

ተስፋዬ ጎይቴ (1979)፡- "በዜና ቱሪዝም የወጡ አጫጭር ልቦለዶች ያነሷቸውም ጭብጦችን መተንተን" ላይ የተሰራ ሲሆን ስለ ጭብጥ ምንነት፣ ጭብጥና ደራሲ ስላላቸው ተዛምዶ እዲሁም ሁለቱ በአንድት ከህብረተሰቡ ጋር ስላላቸው ተዛምዶ ገለጻ ሠጥቷል እኔ ስለ ይዘት ገለጻ በሰጠሁበት ክፍሌ ጭብጥና ይዘት የተያያዘ ፍች ስላላቸው በማያያዝ ማብራሪያ ከመስጠቴ በተጨማሪ ማብራሪያውን መሰረት አድርጌ ልበለደቹን ገምግሜያለሁ፡፡ ይህ ደግሞ የይዘትን ወይም የጭብጥን ምንነት በበለጠ ለማስረዳት ይረዳል፡፡ ተስፋዬም ስለ ልቦለዶቹ ፍሬ ነገሮች ማንሳቱ እና በአጭር ልቦለድ ዙሪያ ማጠንጠኑ እንድንመሳሰል አድርጎናል፡፡ የሚለየን ግን እሱ የጥናቱ ገደብ ሙሉ በሙሉ በጭብጥ ላይ መሆኑና የኔ ደግሞ የልቦለደቹን የቋንቋ አጠቃቀምና ይዘትን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ነው፡፡

ሙሉቀን ታፈሰ (1991)፡- " በቋንቋዎች ጥናት ተቋም የምርቃ መፅሄት በወጡ አጫጭር ልቦለዶች ላይ የይዘት ትንተና" ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው ልቦለዶቹ የተገኙበትን ህብረተሰብ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ስነመልቦናዊ ጉዳዮች አንጸባርቀዋል ወይ የሚለው ላይ ነው፡፡ ይህንም ሲደርግ በህብተሰቡ ዘንድ ያሉ በልቦለዶቹ የተጠቆሙትን ማንኛውም ችግሮች ላይ የመፍትሄ ሀሳቦችንም ጭምር እየሰጠ ነው፡፡ የኔ ጥናት ደግሞ በአቦነህ መድበል ውስጥ የቋንቋ አጠቃቀምንና የይዘት ትንተና ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ነው፡፡ የሚያመሳስለን የልቦለዶቹን ፍሬ ነገሮች ማንሳት ሲሆን የምንለያይበት ደግሞ እኔ ስለ ቋንቋ አጠቃቀም ተጨማሪ ግምገማ ማድረጌ እና እሱ ደግሞ ስለ አጭር ልቦለድ አጠቃላይ ቴክኒክበማንሳቱ ነው፡፡

ደግማዊ ኤጌንዶ (1997)፡ "ሂሳዊ ግምገማ በብርሃን ዳኘ ሸበጥና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች ከአጭር ልቦለድ ዋና ዋና ባህሪያት አንጻር" በሚል የተሰራው ጥናት ይገኛል፡፡ ዳግማዊ በመጀመሪያ የጥናቱን ዳራ፣ አላማ ጠቀሜታ፣ ወሰንና ዘዴ ካዬ በኂላ አስከትሎ በክለሳ ደርሳን ስር የአጭር ልቦለድ ባህሪይ፣ የአጭር ልቦለድ ዋነኛ ባህሪያት ምንነት እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትን ፈትሿል፡፡ ሌላው የብርሃን ዳኘን አጫጭር ታሪኮችን ነጠላ ውጤት ፡ቁጥብነትና ጥድፊያን የዳሰሰበት ክፍል ይገኛል፡፡ በዚህም የታሪኮቹ የቋንቋ አጠቃቀሞች፣ አጠር ባለ መልኩ የልቦለደቹን ፍሬ ነገሮች ማየቱ እና የደራሲውን የቋንቋ ችሎታ ገምግሟል፡፡ ልዩነታቸን ዳግማዊ የልቦለዶችን ባህሪያት

በተናጠል በምሳሌ ማብራራቱ ና እኔ ደግሞ የልቦለዶችን ጭብጦች በመነጣጠል ማሳየት ስለሞክርሁ ሲሆን የሚያመሳስለን ቋንቋንና በመዳሰሳችንና የልቦለዶችን ፍሬ ነገሮች መዳሰሳችን ነው፡፡

ጌትነት ካሳሁን (1995)፡ "የአሳመነው ባሪጋ የትሮይ ፈረስና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች" ከተሰኘው አጭር ልቦለድ መድበል ውስጥ በናሙናነት ስድስት ሥራዎች ወሰዶ ከነጠላ ውጤት፣ ከቁጥብነት እና ከጥድፊያ አንጻር ገምግሟል፡፡ በነዚህ መሰረት ግምገማውን ሲያደርግ የልቦለዶቹን የቋንቋ ሁኔታ፣ የሚስተላልፉት ፍሬ ነገር ና የደራሲውን የቋንቋ ችሎታም ፈትሿል፡፡ ይህ ስራ ከኔው ጋር በመጠኑ ቢሆን ተቀራራቢነት አለው፡፡ የልቦለዶቹን ፍሬ ነገሮች በማንሳቱ፣ የአንድን ሰው አጭር ልቦለዶች በመገምገሙና የደራሲውን የቋንቋ ሁሌታ በማሳቱ ስንመሳሰል፣ እሱ ነጠላ ውጤትንና የልቦለዶቹን ታሪክ በስፋት በመዳሰስ እና እኔ የልቦለዶቹን ቋንቋ አጠቃቀምና ይዘት በስፋት በመገምገም ልዩነት አለን፡፡

ስሜነህ ባይፈርስ (1993)፡ " የኃይለ ኢየሱስ ፈቃዱ አጭር ልቦለዶች ከአጭር ልቦለድ ባህሪያት፣ አላባውንና የአጻጻፍ ዘዴ አንጻር" በሚል የተሰራ ነው፡፡ ስሜነህ ያንድ ብር ዘቢብን፣ ለማኙ አይነሰውርን እና አፈርሳታን የተባሉት አጭር ልቦለዶችን ገምግሟል፡፡ የልቦለዶቹን ታሪክ እየተረከ በመጨረሻ ነጠላ ውጤቶችን ይጠቁማል፡፡ ታሪኮችንም ነጠላ ውጤታቸውን በማሳየት ረገድ የተሳካላቸው መሆኑን አመልክቷል፡፡ ይህን ጥናታዊ ጹሁፍ ከኔው ጥናታዊ ጽሁፍ ጋር የሚያመሳስለው ልቦለዶቹን ነጠላ ውጤት ሲገመግም የዘታቸውን በማየቱ፣ የቃላት ድግግሞሽና ከመጠን ያለፈ ምልልሶች ሲነሳ ስለ ቋንቋ በመተንተኑ ነው፡፡ ልዩነታችን ደግሞ በስሜነህ ሰፋ ያለ ጥናት ያደረገው በባህሪያት፣ በአላባውያና በአፃፃፍ ዘዴ ሲሆን የኔ ጥናት ደግሞ በስፋት ስለ ቋንቋ አጠቃቀምና ይዘት ሰፋ ያለ ፍተሻ ማድርጌ ነው፡፡

ሲሳይ ታደሰ (1974)፡፡ "የተሰፋዬ ገሠሠ አጭር ልቦለዶች ስራዎች በመተከዣ ውስጥ መገምገም፡፡" የሲሳይ ጥናት ስለ አጭር ልቦለድ ጠባይና ምንነት አጭር ልቦለድ ከሌሎች የስነ ጽሁፍ መልኮች በተለይም ከረጅም ልቦለድ የሚለይበትም ጠባይ ሲገልጽ በተጨማሪ ደግሞ የተዋጣና የተሳካ አጭር ልቦለድ ለመጻፍ የልቦለድ ደራሲ ሊያሟላ

የሚገባውን ነገር ይጠቁማል፡፡ ሲገመግም የልቦለዶቹ ጭብጦች የማህበረሱን ህልውና የሚያሳዩ መሆናቸውን እና ነጠላ ወጤትን፣ ቁጥብነትና ጥድፊን ከልቦለድ ጋር አያይዞ ገለጻ አድርጓል፡፡ የሲሳይ ና የኔ ጥናት የሚለያየን እሱ የአጭር ልቦለድና የረጅም ልቦለድ በምን እንደሚለያዩ ማሰሳየቱ እና አጭር ልቦለድ ባህሪያትን የበለጠ ግልጽ አድርጉ ሲያቀርብ እኔ ደግሞ ስለ ቋንቋ አጠቃቀምና ይዘት ሰፋ ያለ ትንተና ማድረግ ሲሆን የሚያመሳስለን አጭር ልቦለድን መሰረት አድርገን የልቦለዶችን ፍሬ ነገሮች ዳሰሳ ማድርጋችን ነው፡፡

## 2.2 ንድፈ ሀሳቦዊ መሰረት

### 2..2.1 የቋንቋ አጠቃቀም ምንነት በአጭር ልቦለድ

ቋንቋ የስነ ጽሁፍ መከሰቻ ብቻ ሳይሆን የስነ ጽሁፍን ስኬታማነት ከሚወስኑት ተግባር ቀደም ተጠቃሽ ነው፡፡ ሊታላለፍ የተፈለገው መልዕክት ያለ አንዳች እክል ለአንባቢው እንዲደርስ ቋንቋው የተሰተካከለ እና ግልፅ መሆን አለበት፡ በመሆኑም በቋንቋ አጠቃቀም ረገድ ጥንቃቄ መውሰድ ተገቢ ነው፡፡

በአንድ ልቦለድ ውስጥ የሚገኙ ገጸ ባህሪያት የሚጠቀሙት ቋንቋ የመኖሪያ አካባቢቸውን እና ያሉበትን ማህበራዊ እርከን የሚያንጸባርቅ መሆን አለበት፡፡ በተለይም ደግሞ የሚኖሩበትን አካባቢ ባህል የተከተለ መሆን አለበት፡፡ Could well, “Illusion and Reality” በተሰኘው መጽሀፍ ቋንቋ ከአካባቢ ጋር ምን ያህል የተቆራኘ እንደሆነ ሲብራራ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ “በስነ አንባብ በዜማ አወራረድ ለአነገር ልዩነት ወይም ቃላት በተለያዩ አካባቢዎች ባላቸው የተለያዩ አጠቃቀም ምክንያት የአንድን አካባቢ ብቸኛ መለያ ሊሆኑ ስለሚችሉ የትርጉም ልዩነቶቸሽ ሊያመጡ ይቻላሉ፡፡ የአንድን ባህል ወሰን የሚያመለክቱት ትክክለኛ አነጋገሮች እነዚሁዘዴዎች ናቸው፡፡” (1958፡196)

ስለዚህ አንድ ደራሲ የሚጠቀመው ቋንቋ የአንድን አካባቢ የአኗኗር ሁኔታ ባህልና ዘዬውን የሚያጸባርቅ ሊሆን ይገባል፡፡ አጭር ልቦለድ አንዱ የስነ ጽሁፍ ዘርፍ ነው፡፡ በመሆኑም የአጭር ልቦለዶልን ባህሪያትን፣ ፍሬነገሮችና ቴክኒኮች ከግብ በማድረስ ለሱ የሚሆኑ የቋንቋ ክፍሎችን ዘይቤና ሌሎችን መምረጥ ይገባል፡ በቃላቱ ቁጥብ መሆን

ይገባል፡፡ በቃላት እና በገጸ ባህሪያት ቁጥብነት ኑሮት የሚጸፍ ነው፡፡ አጭር ልቦለድ ከሌሎች ስነ ጽሁፍ ዘርፎች ሚጋራቸው ባህሪያት እንደ ፍሬ ነገሮችና ቃላት ምርጫ ቢኖርትም በፈጠራ ስራነቱ ከእውነተኛ ታሪክ፣ በዝርውነቱ ከግጥም፣ በቅጽበታዊነቱ፣ በጥፊያው፣ በቁጥብነቱና በነጠላ ውጤት ላይ በማትኮሩ ከረጅም ልቦለድ ይለያል፡፤ አጭር ልቦለድ የግጥምን ያህል ባይሆንም በቋንቋም በኩል ቁጥብ ነው፡፡ ቤትስ The modern short story ብሎ በጻፈው መጽሀፍ አጭር ልቦለድን ከረጅም ልቦለድ ጋር በማነጻጸር እንደሚከተለው ብሏል፡፡ "ለረጅም ልቦለድ 200,000 ቃላት መጠቀም በጣም ጥሩና አስደሳች ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለአጭር በልቦለድም በዚሁ ዘዴና የቃላት መጠን ለመጠቀም መሞከሩ የስድት ወር ህጻንን በረጅም ባርኔጣና ፈር ባለው ኮት ሸፍኖ እንደማፈን ይቆጠራል፡፡ (1941፡16)፡፡ እንደቤትስ አባባል አጭር ልቦለድ በቃላቱ ቁጥብ ነው፡፡ ይህ አጭር ልቦለድ በነጠላ ውጤቶ ላይም እንደሚያተኩ ያሳያል፡፡ በቃላቱ፣ በገጸ ባህሪያቱ፣ በነጠላ ውጤቶች፣ በጥድፊ የሚታወቀው አጭር ልቦለድ 200,000 ቃላት መጠቀም ሰፊ ኮት ና ባርኔጣ ህጻንን ያለ ልክ እንደ ማልስ ነው፡፡ ባጭሩ አጭር ልቦለድ በቃላቱ፣ በገጸባህሪያቱ ድርጊት በጠቅላላው በቃላቱ መጠነርእይ ና በጭብጡ ቁጥብ ነው፡፡

### 2.2.2 የይዘት ምንነት

የልቦለድ ደራሲ አላማ የህብረተሰቡን ምኞትና ፍላጎት የሚያንጸባርቁትን ማለትም ህብረተሰቡ ህላዊ መገለጫዎች የሆኑትን እምነቱን፣ አስተሳሰቡን፣ ብሶቱን፣ ሀዘኑን፣ ደስታውን ወዘተ በኪነታዊ ውበት አላምሮ ለተደራሲያኑ ማቅረብ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ደራሲ ስራውን ሲያዘጋጅ በማህበረሰቡ ውስጥ በመኖር የማህበረሰቡን ችግር ደስታ በአጠቃላይም ዝብርቅርቅ ህይወቱን በወጉ ማገናዘብ መገንዘብ ጠበቅበታል፡፡ ይዘት ምንለውም ይህንኑ መሰረት በማድረግ ደራሲ በህወት ከሚመለከታቸው ከሚታዘባቸው ከተካፈላቸው ገጠመኞች መካከል መርጦ በተቀነባበረና በተቀናጀ መልክ ለተደራሲው የሚያስተላልፈውን መልእክት ነው፡፡ ፒኬሪንግና ሆፐር በስነጽሁፍ መጽሀፋቸው "ይዘት በስነ ጽሁፍ ውሰጥ የሚኖረው ቅርፅ ውስን እና ትርጉም ያለው አተያይ ወይም አጠቃላይ የህይወት አተያይ፣ ደራሲው ከአንባቢያን ጋር ግንኙነት የሚፈጥርበት መንገድ ነው፡፡ ሃሳብን አስተያየትን፣ ስሜት የሚያካፍልበት" ነው ይላሉ፡፡ (1977፡77)

ይዘት የአንድ ልቦለድ ጠቅላላ ጉዳይ የሚሽከረከርበት ሃሳብ ነው፡፡ በልቦለድ ውስጥ ተጽዕኖ የሚኖርበት ክፍል የለም፡፡ ይዘት አጠቃላዩን ስራ የሚያስተባብርና ስለ ህይወት የሚያወሳ ማዕከላዊ ሃሳብ ወይም ጉዳይ ነው፡፡ አጭር ልቦለድም እንደሌሎች ይዘት ያለው ለማበብ ጊዜ የማይፈጅ ነው፡፡

ከሰነጽሁፍ ዘርፎች አንዱ የሆነው አጭር ልቦለድ ከሌሎች የድርሰት ዘሮች የሚለይባቸው የራሱ ባሪያት አሉት፡፡ ነጠላ ውጤት ጥድፊያና ቁጥብነት፡፡ ነጠላ ውጤት ዋናው የአጭር ልቦለድ ባህሪይ ነው፡፡ ሁሉም ነገር በአንድ ተሳስሮ ወደ አንድ ግብ የሚያመራበት፡፡ በአጭር ልቦለድ የሚተረክ ታሪክ ብዙ አይጓዝም፣ ዝርዝር ነገሮችነም አያበዛም፡፡ ፈጠን ፈጠን ብሎ መተረክ አለበት፡፡ እናም ባለመንዛዛቱ፣ ቁጥብና እምቅ በመሆኑ፣ ስብሰብ በማለት ባህሪው ይታወቃል፡፡

አጭር ልቦለድ እነዚህን ባህሪያት በጠባብ ቤት መያዙ ሌሎች የስነ ጽሁፍ ዘሮች የሚስገኙትን ውጤት ሳያጓድል መገኘቱ አንድን የህወት ዘለላ በመውሰድ በብቃት ማቅርብ መቻሉ እምቅነት ባህሪው ነው፡፡ ይህ እምቃትና ቁጥብነት አንድ አለማ ወይም ግብ ለመምታት ነው፡፡ ድርጊቶችን በፍጥነት ተከናውነው በፍጥነት የሚፈጸሙበት፡፡ "ይህ የስነ ጽሁፍ ዘርፍ በባህሪው ቁጥብ ነው፣ አይነተኛና አይቀሬ ጉዳዩችን ብቻ መርጦ እሚይዝ፡፡ እሚጠቀሰው ሁሉ ተጎርዶ ቢቀር እሚያጎድል በሚጨመር ደግሞ በውል ግብ መችነትን የሚያመጣ ነው፡፡" /ዘሪሁን. 1986፡1/

አጭር ልቦለድ ሰፊና ውስብስብ የህይወት ገጠመኞችን የሚያስተናግድበት መድረክ የለውም፡፡ ይልቁንም በአጭር ልቦለድ ገና ሲጀመር የሚቀርበው ነገር ሁሉ ነጠላ ውጤትን ለማሳየት ተብሎ ነው፤ መቅረብ ያለበት፡፡

ከዚህ አንጻር በአጭር ልቦለድ ውስጥ የሚገኝ ይዘት የግድ በባህሪያቱና ለቅርጹ ተገዥ መሆን አለበት፡፡ የአጭር ልበለድ መድረኩም ሆነ የሚወስደው ጊዜ የተመጠነ በመሆኑ የተንዛዛና የተራዘመ ጉዳይን የማስተናገድ አቅም የለውም፡፡ ይልቁንም ጠባብ፣ ነጠላና በጣም የተወሰነ ጉዳይን ብቻ ነው ይዞ መነሳት ያለበት፡፡ስለዚህ የአጭር ልቦለድ ደራሲ ከልደት እስከ ሞት ያለን የህይወት ገጽታዎች ለመተረክ መነሳት የለበትም፡፡ ከአያሌ

የህይወት ልምዶች አንዲቷን ብቻ የሚመለከት ጉዳይን ይዞ ከተነሳ ስራው የተዋጣ ሊሆን ይችላል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የቋንቋ አጠቃቀም በእንቁጣጤ ዕቁጣጣሽ እና ሌሉች ልቦለዶች ውስጥ

### 3.1 የቃላት ምርጫ

#### 3.1.1 የግዕዝ ቃላት

የግዕዝ ቃላት ከግዕዝ ቋንቋ የተወረሱ ቃላት መሆናቸውን እናቀወቃለን የግዕዝ ቃላት ፍቻቸውን ለማወቅ የግዕዝ ቋንቋ ማወቅ ወይም መዝገበ ቃላት መጠቀም ግድ ይላል፡፡ ምንም አይንት የግዕዝ ቋንቋ ዕውቀት የሌላቸው ሰዎች አንድን ልበለድ በሚያነቡበት ጊዜ ሊቸገሩ ስለምችሉ ነው፡፡ ምክኒቱም ደራሲዎች አንዳንድ ጊዜ የግዕዝ ቃላትን ስለሚጠቀሙ ነው፡፡ እንዲሁም የግዕዝ ቋንቋ በአሁኑ ሰአት በብዛት የሚነገሩት በቤተክርስትያን ውስጥ ነው፡፡ እነዚህን ነገሮች ሰበብ አድርገው የግዕዝ ቋንቋ የሚችሉ ገጸባህርያትንሠ ይስላሉ፡፡ በድርሰታቸው ውስጥም የግዕዝ ቋንቋን ይጠቀማሉ፡፡ ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ መሰረት ያደረገው ልቦለድ የግዕዝ ቃላት ይታዩበል ምንም እንኳ የተወሰኑት ከአማርኛ ጋር የተዋረሱና በልማድ የሚታወቁ ቢሆኑም፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ እንዴት ጥቅም ላይ እንዳዋሉ በምሳሌ እመልክት፡፡

"ይኸ ሁሉ በአለም ላይ ያለው <u>እልፍ አዕላፍ</u> ባልና ሚሰት የሚያሳፍር ነገር ሰርቶ ነበር ማለት ነው.....፡፡" /ገጽ፡4/

እልፍ አዕላፍ ማለት ብዙ ማለት

"- የቡና ረከቦት ቀርቦ እስኪነሳ፣ <u>ከአሀዱ እስከ ሁኑ በሰላ፣</u> ከዘበል ባርካ መነሻ እስከ መድረሻ የሚወጋው ስለ ስንትርትርያዋ ባለአውሊያ ሆነ፡፡ "/ገጽ፣ 19፼

ከአሀዱ እስከ ሁኑ በሰላም ማለት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ሚሄዱ ማለት ነው፡፡

"- ጥበብ የተካነችው <u>ቅድስት</u> እስትንፋሷን በዋሽንት . .. . " /ገጽ ፣ 19/

ቅድስት ማለት ተባረከ ማለት ነው፡፡

"- ብሩ ዓበውን በችኮላ ከገማመጠ ባኋላ <u>ዘባተሎውን</u> ተከናንቦ በዳበሳ ወደ ቤንቿ ሥር ገባ ፡፡" /ገጽ፣ 22/

ዘባተሎውን ማለት ጓዙን ማለት ነው፡፤

"- የአእምሮ ገሀነም የብረት በሮች ተዘግተው ገነት ወለል አለች፡፡" /ገጽ፣ 21/

ገሀነም የስቃይ ቦታ ሲሆን ገነት በሰማይ ያለ የፅድቅ ቦታ ነው፡፡

"- ዋሽንት የመላዕክት ቋንቋ ነው፡፡" /ገጽ፣ 20/

የመላዕክት ማለት የጌታ መልክተኞች ነው

ደራሲ አቦይነህ አሻግሬ ከላይ ያየናቸውን የግዕዝ ቃላት በድረሰቱ ውስጥ ተጠቅሞባቸዋል፡፤ እነዚህን ለምን እንደተጠቀመ ሦስቱን የግዕዝ ቃላት ወስደን እንመልከት፡፤

" ይኸ ሁሉ በአለም ላይ ያለው እልፍ አእላፍ ባልና ሚስት ሚያሳፍር ነገር ሠርቶ ነበር ማለት ነው ምነው እዚህ አገር ፍቅር በድብቅ የሚሆነው፣ . . . ዘራፍ!" /ገጽ፣4/

እልፍ አዕላፍ ማለት ብዙ መሆኑን ከዚህ በላይ አይተናል፡፤ በዚህ አረፍተ ነገር ሰለሞን እየታየው ያለ ነገር ብዙ ባልና ሚስቶች እንዳሉ ቢረዳም ሁሉም በድብቅ ትዳር የመሰረቱ መስሎ ይታየዋል፡፡ ይህን እንዲያስብ ያደረገውም አውቶብሱ ውስጥ ያያትን ልጅ ጠይቆ ጥሩ ፊት ሳታሳየው ስትቀር ነው፡፡ ማለት ከበዙ ሰዎች መሀል እሱ ይህን ሲያደርግ የተለየ ነገር ሁኖበት የተጠቀመው ቃል ነው፡፡

" የቡና ረከቦት ቃርቦ እስኪነሳ፣ ከአሀዱ እስ ሁሩ በሰላም፣ ከዘብል ባርካ መነሻ እስከ መድረሻ የሚወጋው ሥለ ስንትረትሪያዋ ባለ አውሊያ ሆነ፡፡" /ገጽ፣19/

በዚህ አረፍት ነገር ውስጥ የግዕዝ ቃሉ ትርጉም ከመጀመሪያው በሰላም እስከሚሄዱ ማለት ሲሆን& የአይኔ አበባ ቡናው ተፈልቶ እስኪያበቃ ትለፈልፋለች፡፡ ይሕ መቀባጠሯም በቁንዝላ ህዝብ አካባቢ ውቃቤ ወይም ዛር የሚባል ሆነባት ብለው ነው፡፡ ደራሲው ይህን ቃል የመረጠበት ምክንያት የመጀመሪያው ሁሉም ሰዎች ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ሥለሷ እያወሩ መሆናቸውን ለማሳየት በአፅንኦት እንዲታሰብበት፡፡ ሌላው የአይኔ አበባ ዛር ወደነሱ እደይተላለፍ በሰላም የቡና ስርአቱ መካሄዱንናእንዴት ይጨነቁ እንደነበር ለማሳየት ነው ብዬ እገምታለሁ፡፡

" ስራ የጀመረችው እንድ በስታ ዋሽንት በመሰራት& ጥናት የቀጸለችው አባቷ ጉልበት ላይ ተቀምጣ ዋሽንት ከከንፈሯ አስጠግቶ "ኡፍ በይበት" ሲላት "አፍ"

በማለት፣ ጥበብን የተካነችው ቅድስት እስትንፋሷን በዋሽንት ቀዳዳ በኩል እየኮረኮረች በመሳቅ፣ በደስታ ሲቃ ፈንድቃ ከአባቷ አንገት ላይ በመጠምጠም ግነባሩን፣ ጉንጩን፣ በመሳም ፍቅርን ከመልካማ ውጤት በማጎዳኘት... በዋሽንት ነው ሰውነቷን መቅረጽ የጀመረችው፡ /ገፅ፣19/

ቅድስት የሚለው ቃል ቀደሰ ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም አመሰገነ፣ ባረከ ማለት ሲሆን ቅድስት የሚለው የሴት ጾታን ለማሳየት ነው ደራሲው ተጠቀመው፡፡ ለማሳየት የፈለገውም የአይኔአበባን የተባረከ ወይም የተቀደሰ እስትንፋሷ የሚያማልል የዋሽንት ድምጽ መፍተሩን ለማሳየት እና ይህም ለህይወቷ ዋና የኑሮ መሰረት ይሆናል ብሎ ስላሰበ፡፡ ከጌታ ተቀድሶ ወይም ተባርኮ የተሰጣትን ትንፋሽ የበለጠ አጉልቶ ለማሳየት ነው፡፡

### 3.1.2 ፍካሬ ቃላት

ፍካሬ ቃላት ከመደበኛ ፍቻቸው በተጨማሪነት የሚይዙትን ፍች የሚያመላክት ነው፡፡ የአንድ ቃል ፍካሬ እንደሚገኝበት አውድ& እንደአገባቡ እና እንደ ማህበረሰቡ ባህል ይወሰናል፡፡ በፍካሬ ፍቻቸው የሚገቡ ቃላተ አንድን ደርጊትና ሁኔታ ከተራና ዘወትራዊ ቃላት አብልጠው በማሳየት ይታወቃል፡፡ ስለዚህም ደራሲው የሚገልጻቸው ሀሳቦች ልቀው እንዲታዩ ፍካሬያዊ ፍች ያላቸውን ቃላት ይጠቀማሉ፡፡

ደራሲ አቦይነህ አሻግሬ ድርሰቱ ውስጥ ፍካቴያዊ ፍች ያላቸውን ቃላት ተጠቅሟል፡፡ እነዚህ ፍካቴያዊ ፍች ያላቸው ቃላት ከመጻህፍ አስረጂ በመውሰድ እንመለከታለን፡፡

"- እህሉን ጠረጰዛው ላይ አዝረከረከው እኮ!" አለች ተኮሳትራ፡፡1 /ገጽ ፣4/

ለመተላለፍ የጠፈጠው የወንድ ዘሩን ነው፡፡

" - በፋብሪካ ጥቀርሻ የጠቆረ ይመስል ያኮረፈና ዶፍ ያለቅሳል፡፡" /ገጽ፣18/

ያለቅሳል ይዘንባል ለሚለው የገባ ነው፡፡ ያርፋና ደግሞ ደምንና ነው፡፡

" መስከረም በጸሀይ ውብ ጥርሷ ከአካባቢው. .. " /ገጽ፣ 1/

ጥርሷ ብርሃኗ ለማለት ነው፡፡

"- ፍም ሞቶ ቀዝቃዛ አመድ ብቻ ይታያል፡፡ " ገጽ፣ 11

እሳቱ ጠፍቶ የሚለውን ተክቶ የገባ ነው፡፤

"- ጭንቅላቱ ውስጥ <u>የሚያዜመው</u> የአዲስ አመት …" /ገጽ ፣ 1/

የሚያስበው የሚለውን ተክቶ ገባ ቃ ነው፡፤

" <u>ካጸዱ</u> በኋላ፣ " እዚህ አምታ… ኬክ ይበላል። ፐሊዝ።" ብለው ጉሯቸአውን ወደ ውስጥ ተሰውሩ። " /ገጽ፣ 2/

ምግባቸውን ከበሉ በኋላ የሚለው በ " ከጸዱ" ተተክቷል።

"- አብረው <u>ስትታመም</u> የመክረሚ ጉዳይና የጥላቸው ሁኔታ በየተራታወሰው።" /ገጽ፣6/ ስትታመም የሚለው ለማስተመሚ ወይም አብራው መቆየቷን ለማሳየት የገባ ነው።

"- አለሚቱን <u>በእምባው</u> መስታወት ውስጥ አየ።" /ገጽ . 12 በአይኑ የሚለው የተካ

"- አለሚቱ <u>ደርቃ</u> እንደቆመች . .. እንባ ግን እፈለቀች። "/ገጽ ፣ 17/ ደንግጣ የሚለውን የተካ

ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ሦስቱን ወስደን ደራሲ አቦነህ ለምን እንደተጠቀበት ለማየት እንሞክር።

" እህሉን ጠረጴዛው ላ እዘረከረከው እኮ!" አለች ተኮሳትራ።

" እንዲያውም ቤተም ተዝረከርካለች። እንሂድና እነደ ወትሮሽ አስተካክይው"

" እህሉን" ማለት በመደበኛ ፍችው ከመሬት ላይ ተዘርቶ በቅሎና ተሰበስቦ የሚገኝ አዝርዕት ነው። ከላይ በተመለከተው አረፍተ ነገር ውስጥ የምናገኘው። <u>እህሉን</u> የሚለው ቃል የገበባት አውድና የሚሰጠው ትርጉም የተለየ ነው። ከመጽሀፍ ታሪክ እነድምንረዳ ሰለሞን በአዲስ አመት ብቻውን መዋል ጨንቆት ከተገናኙም በኋላ ለተወሰነ ሰአት ቢኮራረፉም በኋላ ፍቀርራቸውን እየሞቀ ሄደ። ሲሳሳሙም ስሜቱን መቆጣጠር አልቻለም። በጊዜው በተሠማው ሥሜት የወንድ ዘሩን አፈሰሰ። በዚህ የተገረመችው ንጋት እህሉን አፈሰስከው /አዝረከረከኸው/ አለችው።

"አንዳንዴ ማምሻው ላይ ሰማዩ በፋብሪካ ጥቀርሻ የጠቆረ ይመስል <u>ያኮርፍና</u> ዶፍ <u>ያለቅሳል</u>። ገፅ ፣18

"ያልቅሳል" ማለት በመደበና ፍችወ ጸታው ወንድ የሆነ ሰው እያለቃሰ የሚያዝን/ በእንባ የሚተናነቅን ሰው ያሳያል፡፡ ከላይ በተመለከትነው አረፍተ ነገር ውስጥ የምናገኘው " ያለቅሳል" የሚለው ቃል ከገባበት አውድና የሚሰጠው ትርጉም የተለየ ነው፡፡ ይህም በወቅቱ የሚዘንበውን ጠንካራ ዝናብ ለማሳየት ነው ደራሲው የተጠቀመበት፡፡ "ያኮርፍና" ማለት በመደበኛ ፍችው የተናደደ ወይም የተቆጣ ሰውን ያሳያል፡፡ በዚህኛው አውድ ግን ዝናብ ሊዘንብ ሲቃረብ ከበድ ያለ ዳመና ይታያል፡፡ይህን ጠንካራና ከበድ ብሎ የመጣውን ዳመና ለማሳየት ወይም በጊዜው የነበረውን ከባድ ዳመና የተለየ ትኩረት ለመስጠት ደራሲ ይህን ቃል የተጠቀመበት ይመስላል፡፡

> "መስከረም በጸሀይ ውብ ጥርሷ ከአካባቢው ፍጥረታት ጋር በፈገግታ ስታወጋ ሁለመናው ፈገግ አለ፡፡" /ገጽ፣1/

" ጥርሷ/ ማለት በመደበኛ ፍችው ሴት የሆነችን ሰው አካል ክፍል የሆነውን ጥርስን ያሳያል፡፡ ከላይ በተመለከተው አረፍተ ነገር ውስጥ የምናገኘው " ጥርሷ" የሚለው ቃል የገባበት አውድና ሚሰጠው ትርጉም የተለየ ነው፡፡ ይህ ትረጉምም የመስከረምን የጸሀይ ብርሃን ለማሳት የገባ ነው፡፡ ደራሲው ይህን ቃል የመረጠበት ምክንያት መስከረም ወይም በእኛ ሀገር አቆጣር አዲስ አመት ላይ የሚወጣው የጸሀይ ብርሃን ንጋት ላይ በጣም ደስ እንደሚል የሚያሳይ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ለማሳት የተፈለገው በአዲስ አመት ዋዜማ ላይ ሰለሞን ብቸኛ መሆን እና ይህ ብቸኝነቱም በውስጡ ሲያስባት የነበረእችው ቆንጆ ውበት ለማሳየት የተቀመበት ነው፡፡

### 3.1.3 ዘዬ ቃላት

ዘዬ ቃላት የአንድን ማህበረሰብ አነጋገር ባህል ወይም የንግግር ቋንቋን የሚያሳይ ነው፡፡ በአንድ ቋንቋ ውስጥ የተለያዩ ዘዬዎች አሉ፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ብናይ እንኳን የጎጃም፣ የጎንደር፣ የወሎ ዘዬዎች ይገኛሉ፡፡ ቋንቋው የሚነገርበት ቦታ ስለሆነ የሚጠቀሙባቸው ዘዬዋች የተለያዩ ናቸው፡፡ በደራሲ አቦነህ መድበል ውስጥ የተጠቀሱ ዘዬዎችን እንዲኪተለው እንመክከት

> "ታዲያ ከሰፈር ቁንጣ አሽከሮች ጋር ለጫወታ…" /ገጽ ፣ 19/ ቁንጣ የጎጃም ዘዬ ሲሆን አሽከር የጎንደር ዜዬ ነው፡፡

“ተየሀ ቀድሞ ምክሮ ያልተሳካለትን ደግሞ ሲሞክር ወደ ላይ አንሰቶ ሊያፈርጣት ሆዱ፡ ከበደበችው፡፡” /ገጽ፣13/

ተየሀ የወሎ ዘዬ ነው፡፡

“ዳና ነው፡ ብርድ ማታ አሳሙማል፡፡” /ገጽ፣2/

እነዚህ ሁለቱ ቃላት በብዛት በጎጃምና በጎንደር አካባቢ የሚዘወተሩ ቃላት ናቸው፡፡

እነዚህ ላይ ያየናቸው ምሳሌዎች የተለያዩ ክልሎችንና አካባቢዎችን የሚወክሉ ናቸው፡፡ የትግሬ፣ የአማራ፣ የደቡብ፣ የኦሮሞ ዘዬዎችን ደራሲው ሲጠቀም በተለይ ደግሞ ከአማራ የወሎ፣ ጎጃምና የጎንደር ዘዬዎች ተጠቅሟል፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉተን እንይ፡፡

“ታዲያ ከሰፈር ቄንጣ አሽከሮች ጋር ለጫወታ ጣና ዳር ወርዳ ስንትሮትርያዋን ስትለቅበት ማዕበሉ ጸጥ ይልና… አሳዎችን ነጭ አምራዎች አናታቸውን ከውሃ ብቅ አድርገው ጣናን ምስማር ችምችም ያለበት ጣውላ ያስመስሉታል፡፡” /ገጽ19/

በዚህ አረፍት ነገር ላይ የምናገኛቸው ዘዬዎች “ቄንጣ” ና “አሽከሮች” የሚሉት ቃላት ሲሆን እኒዘህ የተገለጹትም አለሚቱ ልጁ መሆኗን እና ከሰፈር ትንሽ ልጆች ጋር ለጨዋት ወደ ጣና እንደምትሄድ ያሳያል፡፡ ስለዚህ ደራሲው በጎጃም አካባቢ የሚነገሩትን ዘዬዎች “ቄንጣ” ትንንሽ ወይም ታዳጊ “አሽከሮች” ልጅ የሚሉትን ውክልና በሚነገሩበት አካባቢ ሰይሞ አስፍሯቸዋል፡፡ አሽከር የሚለው ዜዬ በብዛት በጎንደር አካባቢ የሚዘወተር ዘዬ ቢሆንም ደራሲው ቁንዝላና ጎንደር በጣና ሀይቅ ሚለያዩ እና በባረካ ሁሴ መገንናኘታቸውን ለማሳየት በአለሜቱና በሰፈረ ልጆች አማካኝነት ገልጾታል፡፡

“ታየሀ ቃደም ሞክሮ ልተሳካለትን ደግሞ ሊሞክር ወደ ላይ አንስቶ ሊያፈርጣት ሆጵ፡ ከበደችው፡፡” /ገጽ 13/

በዚህ አረፍት ነገር ላይ የምናገነው ዘዬ “ተየሀ” የሚለው ቃል ሲሆን ይህ የተገለፀውም ጎንጃባ ከአለሚቱ ጋር በሚያደርገው አለመግባባ ወቅት የአለሜቱን አክስት ንግግር ያሳያል፡፡ የአለሚቱ አክስት መናገረ የፈለገችው ተየሀ ሚለው ልክ እንደትክክለኛ ትርገሙ “ አየሀ” እንደ ማለት ብላ ነው፡፡ ይህም በብዛት የወሎ አካባቢ ዘዬ ነው፡ አልፍ አልፎም በጎንደር አካባቢ ይነገራል፡፡

ሌሎች ዜዬዎችም ማለት አሳምሚው፣ ዳና ጎጃምን፣ ቴፍቷል ደቡብን፣ ዋይትግን፣ ወክለው የተጻፉ ዘዬዎች መሆናቸውን ከዘህ በላይ አይተናል፡፡

### 3.1.4 የእንግሊዘኛ ቃላት

ደራሲው ከውጭ ቋንቋዎች የወሰዳቸው የእንግሊዘኛ ቃላት በድርሰቱ ውስጥ ይገኛሉ ቃላቱ በተገቢው ቦታ ገብተው የገጸባህሪያትን ማንነት የኑሮ ሁኔታ፣ የትምህርት ደረጃና ለመልክቱም የተለየ አጽንኦት እንዲሰጣቸውብሎ የተጠቀመባቸው እንግሊዘኛ ቃላት አሉ፡፡ ይሁን እንጅ ለደራሲው የታየው ለአንባቢው ሳይታዩ በመደበኛ ቋንቋው ውስጥ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ቃላት በመቀላቀላቸው በልቦለዱ ማግኘት የፈለጉትን ነገር ወይም ሀሳብ የሚያፈርሱ ስህተቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ በመድበሉ ውስጥ የተገኙ የእንግሊዘኛ ቃላትም የሚከተለውን ይመስላሉ፡፡

> “ ሀፒ ኒው ይር … ሰለሞን፡፡ “ አሉ ማዳም … በአርጅና የጎበጠው ወገባቸውን ከመስኮቱ ክፈፍ ወጣ አደርጓቸዋል፡፡ /ገጽ፣2/
>
> የተሰመረበት ቃል ትርጉም መልካም አዲስ አመት ማለት ነው፡፤

የሁለቱ ገጸባህሪያት ሰለሞንና ማደም በአዲስ አመት ላይ የብቸኝነት ሀሳብ ውስጥ መሆን አስጨንቋቸዋል፡፡ በመሆኑም ማዳም ከቤታቸው ውስጥ ቁጭ ብለው ይሰሙት የነበረው የተለያየ አይነት ድምጽ የመድፍ፣ የጥይቱ፣ የጥንብዶቹ ወግ፣ የልጆቹ ሆያ ሆዬ ሁሉ ብቸኝነታቸውን አባብሶት ነበር፡፡ በዚህ ሰዓት ከቤታቸው ሲወጡ ሰለሞንን በማየታቸው በደስታ ስሜት ነበር “ሀፒ ኒው ይር” ሰለሞን ያሉችው፡፡ ስለዚህ ደራሲው የአዲስ አመትን ድባብ ለማሣየት ነበርሀፒ ኒው ይር የሚለውን የእንግሊዘና ቃል የተጠቀመው፡፡

> “ብሩ ዳቦውን በችኮላ ከገማመጠ በኋላ ዘባተሎውን ተከናንቦ በደስታ ቤንቿ ስር ገባ፡፡ ዋሽንቱንም አንገቱ ስር አጋደመ፡፡ ተጋደመ፡፡”/ገጽ፡22/
>
> ትርጉሙ አግዳሚ ወንበር ማለት ነው፡፡

የብሩ ብልቢሌን የስቃይ ኑሮ፣ የሚያድርባቸውን ቦታዎች ለማሳየት ነው፡፡ ደራሲው ይህን ቃል የተጠቀመው፡፡ ብሩ ማየት የተሳነው ስለሆነ በዳበሳ ያገኘውን አግዳሚ ወንበር

እንደመጠለያ ተጠቅሞ ይተኛበታል እንዲሁም ለልመና ዋሽንቱን እየነፋ ቁጭ ይልበት የነበረውን ያሳያል፡፡

ሌሎች በመድበሉ ውጥ ያሉ የእንግሊዘኛ ቃላትን ለመዘርዝር ያህል

"- አብነት ስለምትኖር ሆስተስ እህቷ ለማናገር የፈጀው ጉልበት እና ጊዜ… "/ገጽ፡2/ ትርጉም አስተናጋጁ

"- ዳና ነው፡፡ ብርድ ማታ አሳምሟል፡፡ አልድ ፕሮብሌም፡፡" /ገጽ፡ 2/ ትርጉም የቆየ ችግር

"- አንቴ ወታትኖ - ቶል ፣ ሀንድሰም፡ ሆሊደይ ጎደኛ ያስፈልጋል . . . አንቴ፡ ንጋት እዚህ ቴፍቷል፡፡" /ገጽ፡ 2/ ትርጉማቸው የሚያምርና ክብረበአል ናቸው፡፡

" ገመድ ስትጫወት ሌትር ከደረቷ ሹራብ ወድቆ ጂምላስቲክ አስተማሪ ስላገኙት፡፡" /ገጽ፡ 16/ ትረጉም ሌተር ደብዳቤ፣ ጂምናስቲክ አኩሮባት እና ሌሎችንም የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎች ማለት ነው፡፡

## 3.2 የዜይቤ አጠቃቀም

"ዘይቤ፣ ትኩስነት ና ጥንካሬ ለመስጠት ሲባል ከመደበኛው ቃት ፍች ወይም የቃላት አደራደር ሥርአት ሆነኝኝ ብሎ ማፈንገጥ ነው፡፡" /ዘረሁን 1996፡105)

አቦነህ በድርሰቱ ውስጥ የተለያዩ ዘይቤዎችን እንደሰውኛ፣ አነጻጻሪ ተለዋጭ ንቡር ጠቃሽና እንቶኔ ዘይቤዎችን ተጠቅሟል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት የሚዳሰሱት በደርሰቱ ውስጥ በብዛት ሚገኙትን ሦስቱን ብቻ ነው፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 3.2.1 አነጻጸሪ ዘይቤ

አነጻጻሪ ዘይቤ ሁለት የተለያዩ ነገሮችን በመውሰድ በተመሳሳይ የማነጻጸሪያ መንገድ ነው፡፡ "ይህ ዘይቤ ሁለት ነገሮችን፣ ሀሳቦችን፣ ድርገጊቶችን ወዘተ በማናጻጸር ወይም በማወዳደር የሚፈጠር ዘይቤ ነው፡፡" /ዘሪሁን 1996፡ 107/

በዚህ አጭር ልቦለድ መድበል ውስጥ ደራሲው ሊገልጸው የፈለገውን ሀሳብ አጉልቶ ያሳይልኛል ብሎ ባሰበባቸው ቦታዎች አልፎ አልፎ ተጠቅሞባቸዋል፡፤ ለዚህ ዋቢይ ሆን ዘንድ ከልበለዱ ምሳሌዎችን በማጣቀስ እንመልከት፡፡

" አለሚቱ የጎንጀባን ቁንጮ ይዛ በቀንድ እንደሚስብ ፍየል እየጎተተችው ወደ ቤት ወስዳ መጥረጊያ ሰጠቻው፡፡" /ገጽ ፡12/

“እንደ ሞተ ሰው መሆንን መረጠ፡፡ “ ሞትኩ!!” ብሎ ሞቱን አወጀና ባለፈው ፋሲካ ጎረቤታቸው እንደታረደው በግ ተንፈራገጠ፡፡” /ገጽ፡ 13/

“ እስቲ በሰማም ብዬ ልጀምር ሰላምታ

ለተቀመጥሽነት ላለሸበተ ቦታ

ጥርስሽ የሚመስለው የጊደር ወተት

ጸጉርሽ የሚመስለው የሐር ጉኝጉኝ . . . “/ገጽ ፡16/

“አንዳንዴ ማምሻው ላይ ሰማዩ በፋብሪካ ጥቀርሻ የጠቆረ ይመስል ኮርፋና ዶፍ ለቅሳል፡፡” /ገጽ፡ 6/

“በነጭ የሀገር ልብስ ጸደይ የመሰሉ ባልና ሚስት ቢጤዎች እጅ ለእጅ ተያይዘው ሽቅብ ይወጣል፡፡” /ገጽ ፡ 8/

ከላይ ከተዘረዘሩ መካከል ሦስቱን ለማብራራት ስሞክር የሚከተለውን ይመስላል፡፡

“አለሚቱ የጎንጀባን ቁንጮ ይዛ በቀንድ እንደሚሳብ ፍየል እየተተችው ወደ ቤት ወሰዳ መጥረጊያ ሰጠችው፡፡” /ገጽ፡ 2/

ከላይ የተሰመረበት ቃል አነጻጻሪ ዘይቤ ነው፡፡ በዚህ ተገለጭ የገጸባህሪው ቁንጮ ሲሆን ገላቹ የፍየል ቀንድ ነው፡፤ ገላቹ ተገላጩን አጉልቶና አድምቆ ማቅረብ ችሏል፡፡ በመሆኑም ደራሲው ሀሳቡን በሚገባ ለማስተላለፍ ችሏል፡፡ ተገላጩ የሰው አካል ሲሆን ገላጩ ደርግሞ ፍየል የሚባል እንስሳ ቀንድ ነው፡፡ ይህ ንጽጽር ገጸባህሪው የተሳለበትን ባህሪይ የበለጠ አገሁልቶና ምስል ሰጥቶ ማሳየት የቻለ ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡ በመሆኑም ደራሲው የተጠቀመው ይህ ዘይቤ ተገቢ እንደሆነ ለማየት ተችሏል፡፡

“ እስቲ በሰማም ብዬ ልጀምር ሰላምታ

ለተቀመጥሽበት ላላሸበት ቦታ

ጥርስሽ የሚመስለው የጊደር ወተት

ጸጉርሽ የሚመስለው የሐር ጉንጉን . . .” /ገጽ ፡16/

ከላይ የተሰመረባቸው ሀረጋት አነጻጻር ዘይቤዎች ናቸው፡፡ በዚህ ዘይቤ ተገላጩ የአለሚቱ ጥርስ ና ጸጉር ናቸው፡፡ ገላጮቹ ደግሞ የጊደር ወተትና የሀር ጉንጉን ናቸው፡፡ ገላጮቹ ተገላጮቹን አጉልተውና አድምቀው ማቅረብ ችለዋል፡፡ በመሆኑም ደራሲው ትክክለኛ አነጻጻሪ ዘይቤን ተጠቅሟል፡፡ ተገላጮቹ የሰው አካል ክፍል የሆኑት ጥርስንና ጸጉርን ሲሆን ገላጮቹ ደግሞ ከእንሰሳት የጊደር ወተትና ከቁሳቁስ ሀር ጉንጉንን ናቸው፡፡ ይህ ንጽጽር ገጸ ባህሪዋ የተሳለችበትን ባህሪይ /ውበት/ የበለጠ

አጉልቶና ምስል ሰጥቶ ለማሳት የቻለ ነው፡፡  በመሆኑም ደራሲው የተጠቀመው ይህ ዘይቤ ተገቢና ለአለሚቱ የተለየ ውበትን በመስጠቱ ተገቢ እንደሆነ ለማየት ተችሏል፡፡ ስለዚህ በአጠቃላ ከላይ ያየናቸው ሰማይን በጠቀርሻ፣ ባልና ሚስት በጻደይ፣ ኮረዳዋ በሽቦ ጎንጀባን እንደ ሞተ ሰውና እንደታረደ በግ፣ ቁንጮውን በፍል ቀንድ አድርጎ በማነጻጸር የተጠቀመበት ዘይቤ ደራሲውን ዝይቤ አጠቃቀሙ የተዋጠለት ያሰኘዋል፡፡

### 3.2.2 ሰውኛ ዘይቤ

ሰውኛ ዘይቤ ሰው ላልሆነ ነገሮች የሰውን ባህሪይ በመስጠት እንደሰው ነገሮችን ሲያደርጉ የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ በአቦነህ ድርሰት ውስጥ የተወሰኑ ሰዎኛ ዘይቤዎች አሉ፡፡ ይህ ሲነጻጸር ደራሲው የተጠቀመው ሰውኛ ዜይቤ ከሌሎች ዜይቤዎች ባነሰ መልኩ የሚገኝ ነው፡፡ ይህንም እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

"ከመስኮቱ አጠገብ ብቸኛ የፅጌሬዳ ተክል ሁለት <u>እምቡጦች ተቃቅፈው</u> እንቅልፋቸአውን ይለጥጣሉ፡፡" /ገጽ፡ 1/

"የዋሸንቱን ድምፅ ከሩቅ እደሰማች የውስጥ አካሏ በፍንደቃ ንብንጥረ ነገር ተመጥላ፡፡ የዋሸንቱ በጅናትና፡፡ /ገጽ፤2/

ብቻ <u>ተፈጥሮ ረቂቅነቷን</u> ለራስዋ መታረጋግጥ በታሪካቸው መሀል ዥዋዥዌ እተሜዎተች ልትስ እቅዷን ነደፈቻብኝ፡፡  /ገጽ ፡ 25/. ይ ተሰለምን የተሰጠ ነው፡ ፤

"ሰማዩ መድፋን ሊተኩስ ሲል ከሚሰጠው ብርሃን ማስጠንቀቂያ ሌላ ሲያይ የሚችለው የሚኪናው የውስጥ አካል ብቻ ሆነ፡፡" /ገጽ 35/

" በፈንታው ኮረዶች አዳዲስ ደማቅ ናይለን ቀሚስ ለብሰው በአንድ <u>ከበሮ አዛዥነት</u> " አበባ ሆይ፡ ለምም፡ ፣" እያሉ ደጅ አዳሪውን የሆስቴሉን ዘበኛ ከበውይ ዘፍናሉ፡፡"/ገፅ፤ 6/

ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት መካከል የመጀመሪያ ሁለቱን እንመለክት፡፤ የመጀመሪያው የተሰመረበት አረፍተ ነገር ውስጥ "እምቡጦች" የሰው ልጅ ባህሪይ የሆነውን መተቃቀፍንና እንቅልፍ መተኛትን ተሰጥቷቸዋል፡፡ ይህም እምቡጦች በወጣትነት እድሜ ያለን የሰውን ልጅ ዕድሜ ወክሉና የኑሮ አለመመቸት ገጥሟቸው በየቤቱ ታዛ ወይም ጥግ ሚያድሩትን ለማሳትየት ነው የገባው፡፡ ደረሲውም ይህን የተለየ አትኩሮት በመስጠት በተገቢው ቦታ አስገብተውታል፡፡

በለሁተኛው ላይ ከምንመለከተው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት "ተፈጥሮ" የሚለው ቃል የሰው ባህሪይ ሆነውን ቿዋቿዌ መጫወትናመሳቅን ተሰጥቷታል ይሰጣል፡፡ ይህም ተፈጥሮ ሃይሏን ረቂቅነቷን ልታረጋግጥ ሌላ ነገር ባደረጉ ታሪከኛ ሰዎች መካከል የምታደርገውን ድርጊት ያሳያ፡፡ ስለዚህ ደራሲው ይህን ዘይቤ በተገቢው ቦታ አስገብተው ለተፈጥ የተለየ ውክልና ሰጥተው ማስገባታቸው ተገቢ ነው፡፡

### 3.2.3 ተለዋጭ ዘይቤ

ተለዋጭ ዘይቤ አንድ ልንገልፀው የፈለግነው ነገር ምሰላዊ ሆኖ እንዲታይ በአካል ወይም በባህይ ከሚይመሳሰለው ሌላ ነገር ጋር ያለው ግንኙነት ዝምድና በመፈለግ የተመሳሰሉ አድርጎ የሚያቀርብ የዘይቤ አይነት ነው፡፡ ይህ ዘይቤ ከአንጻጻሪ ዘይቤ የሚለየው ይመስል፣ እንደ ሚሉ ቃላትን ሰለማይወስድ ነው፡፡ ደራሲው የተጠቀመው ተለዋጭ ዘይቤዎችም የሚከተለውን መስለሉ፡፡

"መስከረም <u>በጸሀይ ውበ ጥሏ</u> ከአካባቢው ፍጥረታት ጋር በፈገግታ ሰታወጋ ሁለመናው ፈገግ አለ፡፡" /ገጽ፤ 1/

"አንዳንጼ ማምሻው ላይ ሰማይ በፋብሪካ ጭቀሪሻ የጠቆረ ይመስል ያከርፍ ና ዶፍ ያለቅሳል፡፡ ሲያስኘው ደግሞ<u> ደመና መጋረጃውን ገፎ</u> ፈገግ ይላል፡፡ በፒያሰ መንገድ ኮሬንቲ ብርሃን ወጋገንም ይፈካል፡፡" /ገጽ ፣18/

"እንደዚያ ቀጭን የነበረችው ዕንቡጥ ፅጌሬዳ እንደ ሽቦ በመጠንከሯ ግን አልተቻላቸውም፡፡ <u>ሚዳቋ ነበር የሆነች</u>፡፡" /ገጽ 18/

"እየደራ እየሞቀ የነበረው ዘፈን ባንጼ እረጭ እንዳለ የሰፈሩ ልጆች በጃልሜዳዎቹ እተባበሩ ወደ ጎንጀባ ቤት በሩጫ ገቡ፡፡ <u>የጠጠር ዝናቡ በያራው ላይ ዘነበ</u>፡፡" /ገጽ፣ 15/

"በልቡ ያሰበውን አለሜቱ ሰምታበት እንደሆነ ለማጣራት ከጠረጼዛው ስር ሁኖ ቀና ብሎ አያት <u>በእንባ መስታወት ውስጥ</u>፡፡ "/ገጽ ፡ 13/

"ሲያቸው መልው ያዩታል፡ ፤አንደበታቸውን ይሳከፍቱ በልባቸው አንተ ብቸኛ ሰነፍ፡፡ እያሉ የሚያፈጠበት መሰለው፡፡ ከዓይናቸው ለመሸሽ መብራቱን አጠፉ፡፡ አንሶላውን ተከናንቦ ኩርምት ብሎ ተኛ፡፡" /ገጽ ፣1/

ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩ ሁለት ለማብራራት ስሞክር ሚከተለውን ይመስላል፡፡ "ሚዳቋ ነበር ሆነችው" ሚለውን ስና የይኔአበባን የተባለቸው ሰው ናት በሚዳቋ የተለወጠችው ወይም የዱር እንሰሳዋን ጸባይ በሙሉ ለሰብአዊ ፍጡሯ ያይኔአበባ ተለውጡላታል፡፡

ይህም ደራሲው ለማሳት የፈለገው የአይኤአባባን ጥንካሬ፣ የአልበገሬ ባይነትና በቁንዝላ ህዝብ ሀሜት ከዋሽንት ችሎታዋ ያልታገደች መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ ስለዚህ የእንስሳት ጸባይ ለሰው ልጅ ለሆነችው የተለወጠው ወይም የተሰጠው፡፡

ሌላው “ደመና መጋረጃውን ገፎ” የሚለው ሀገግ ደግሞ ተለዋጭ ዜይቤን እንደሚያሳይ የጠቀስሁት ነው፡፡ በዚህ ውስጥም በተለምዶ ሰማ ላይ የሚታይ ጉም፣ ጭጋግና ደመና የሚባሉት ይታይበታል፡፡ ነገር ግን መጋረጃ በሚባል ሰው ሰራሽ ነገር ተለውጦ ይታያ፡፡ ስለዚህ ሰማይ ላይ የሚታዩ ደመናዎች መጋረጃ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ነገር ግን ደራሲው በጊዜው የነበረውን የዝናብ ክብደት ለማሳት እና ከዘነበ በሃላ ወዲያው መባራቱን ለማሳት ነው፡፡

በአጠቃላይ ደራሲ አቦነህ የተጠቀማቸው ዜይቤዎች ሊገልጹ የፈለጉትን ሀሳቦች በተሻለ መልኩ ለማቅረብ ረድተውታል፡ እነዚህም ሰውኛ ተለዋጭ አነጻጻሪ ዘይቤና ሌሎችንም ለተለየ የአገላለጽ ዘዴ ተጠቅሞባቸዋል፡፡

## 3.3 በቋንቋ አጠቃቀም ረገድ የታዩ ድክመቶች

### 3.3.1 የቃት ድረታ

በአንድቃል ሊተላለፍ የሚችለውን ሀሳብ፣ ሀሳቡን በተሻለ የስተላልፍልኛል በማለት ሁለትና ከዚያ በላይ ሆኑ ቃላትን በመደራረብ መጠቀም ነው፡፡ የቃላት ድረታ የተባለው፡፡ አውቀወም ሆነ ሳያውቁ አንድ አይነት የሆኑ ቃላትን በመደጋገም መጻፍንም ያካትታል፡፡ እነዚህ ድረጊቶች ደግሞ መወፈድ አለባቸው፡፡ ምክኒያቱም ጥሩ ደራሲ በቃላት አጠቃቀሙ ረገድ በተለይ በአጭር ልቦለድ ቁጥብ መሆንና ለማስተላፍ ለሚፈልገው መልዕክት ይበጀኛል የሚላቸውን ቃላት መምረጥ አለበት፡፡ ለምሳሌ ያህል፡-

1. “- ዷዷ! ዷ!ዷ!ዷ!ዷ- -- መድፉ .ገጽ፣ 1/
   መድፍ ተተኮሰ ማለት ሲቻል፤.
2. “- ከዚያ፣ ከዚያ፣ከዚያ ---“ /ገጽ 2/
   ከዚህ ቀጥሎ ብሎ አንድ ጊዜ ብቻ መጠቀም ሲቻል
3. “- አትበለኝ፣ አትብለኝ፣ አትበለኝ፣ ---“ /ገጽ፣ 6/
   አንድ ጊዜ ብቻ አትበለኝ ማለት ይቻል ነበር፡፡

4. "- ቋ! ቋ!ቋ - - - አደረገችው።" /ገጽ ፣ 14፣17፣18፣19/
   በኩርክም መታችው ለማለት ተጠቀመው
5. "- ድው ፣ ድው፣ ድው ---" አለ የልብ ነገሪት።" ገጽ 14/
   የልብ ምቱን መጨመሩን ለማሳት የተጠቀመው።

6. "- ፍሉሉ - - - " አደረገ ዋሽንቱን /ገጽ 23/
   ዋሽንቱን ነፋ ለማለት ተጠቀመው።
7. ፑ-ሉ-ሉ-ሉ-ሉ---"/ገጽ ፣ 24/

ዋሽንቱን በተከታታይ መንፋቱን ለማሳየት። በእንቁጠ ዕንቀጣጣሽ እና ሌሎች ልቦለዶች በሚለው መድበል ውሥጥ አሰልች በሆነ መልኩ ከዚህ በላይ ከጠቀስናቸ ቃላት በብዛት መደጋገ የታየባቸ አሉ ከዚህ መድበል ወስጥ ጎልተው የታዩት መጀመሪያው አለሜቱ ጎንጀባን ሁሌ እራሱን ስለምትታው ይህ ለማሳት "ቋ፣ቋ፣ቋ - -- - " ፣ በሁለተኛ ደረጃ በድርሰቱ ውስጥ በብዛት ተደጋግሞ የሚገኘው " ፑ-ሉ-ሉ-ሉ---" የሚለው የብሩ ብልቢሌ ዋሽንት መንፋትን ለማሳየት እና በመጨረሻ በብዛት የተደጋገመው አትብለኝ፣ አትብለኝ፣ አትበለኝ ---" የሚለው የንጋትን አነጋገር ነው። ሰለሞን ንጋትን ከእድሜዋ መብሰል ጋር አያይዞ እመቤቱ ሲላት አረጀሽ እያለኝ ነው መስሏት፣ እመቤቱ አትበለኝ ለማለት በብዛተ ተደጋግሟል፡፤

በዚህ መልኩ የቃላት፣ የድምጾች፣ የሀረጋት፣ መደጋገም አንባቢ እንዲሰለች ያደረጋል። ከዚህ አልፎ አንብቦ ሊረዳ የፈለገው ፍሬ ነገር እንዳይገነዘብ ሊያደርጉ ስለሚችሉ መስተካከል ያለባቸው ይመስለኛል። ስለዚህ ከላይ ያየናቸው ቃላት በቅደም ተከተል ከአነደኛው ጀምሮ ሲታኮስ፣ አትበለኝ፣ በኩርኩም፣ ሲፈነዳ፣ ሲነፋ፣ የጥላሁንን የሚሉትን ቃላት አንዴ ብቻ ቢጠቀም የተሸለ ይሆናል። አንባቢንም ላያስቸግር ይችላል ብዩ እገምታለሁ።

### 3.3.2 ጉራማይሌ ቋንቋ

ጉራማይሌ ቋንቋ የሁለት የተለያዩ ቋንቋዎች ቃላት በመደባለቅ መጠቀም ሂደት ነው። ይህንን አይነት ቋንቋ መጠቀም ጠቀሜታም ጉዳትም አለው። ጠቀሜታው ደራሲው ስለ ገጸባህሪው ማንነት ወይም ማሳወቅ ስለፈለገወ ጉዳይ የተለየ ትኩረት ለመስጠት ሊሆን

ቢችልም የተወሰኑ አንባቢዎች ያነገር ያለመረዳት ችግር አለው፡፡ በዚህ መድበል ውስጥም የዚህን አይነት የቋንቋ አጠቃቀም እናገኛለን፡፡ ይህንንም በተለያዩ አስረጂዎች በመውሰድ እንመልከት፡፡

"- <u>ሀፒ ኒወ ይር</u> ሰለሞን ---"/ገጽ ፤2/

የእንግሊዘናን ቋንቋ ከአማርኛ ቋንቋ ጋር ባንድ ጊዜ

"- <u>ሆሊዴ</u> ጉደና የስፈልጋል፡፡" /ገጽ፣ 2/

እንግሊአኛና አማርኛ በአንድ ላይ የተጻፉ፡፡

<u>"-እልፍ አዕላፍ</u> ባልና ሚስት የሚያሰፍር ---- " /ገጽ፣ 4/

አማርኛና ግዕዝ በአንድ የተጻፈ

"- <u>ዘባተሎውን</u> ተከናንቦ----"/ገጽ፣ 22/

አማርኛና ግዕዝ በአንድ ላይ

"- አንቴ <u>ወተትኖታል ሀንድሰም</u> ----"/ገጽ፣ 2/

አማርኛ፣ ከምባተኛና እንግሊዝኛ ቋንቋ በአንድ ላይ፡፡

"- <u>ሌተሯ</u> ወደቀ ---"/ገጽ ፣ 16/ አማርኛና እንግሊዘኛ በአንድ ላይ

<u>"-በጀንትራቮልታዊው ጸጉሯ</u> --- /ገጽ፣22/

"-<u>ቤንቿ</u> ስራ---"/ገጽ---"/ገጽ፣22/

ሁለቱም የአማርኛና የእንግሲዝኛ ቋንቋ በአንድ ላይ የተጻፋ ናቸው፡፡

ከላይ በጠቀሱት ሰረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው የእንግሊግሊዝኛና የግዕዝ ቃላት ናቸው ይህ መሆኑ ብዙ ጊዜ የገጸባህሪያትን ማንነት በተወሰነ ደረጃ እንድናወቅ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት በመድበሉ ውስጥ ከሚገኙ የውጭ ቋንቋዎች አብዛኛዎቹ ናቸው፡፡ የገጸ ባህሪያት ማንነት በተወሰነ ደረጃ እንድናውቅ ማድርጉ ጥሩ ጎን ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ሆኖም ግን ከአንባቢው ወገን ሁነን ስንመለከታቸው የቃላቱ መብዛት የሚያመጣው ተጽእኖ አለ፡፤ እንደሚታወቀው ሁሉም አንባቢ እኩል የዕውቀት ደረጃ አለው ማለት አይቻልም፡፡ እንግሊዝኛ ቋንቋ ወይም ግዕዝ የማይገባውን አንባቢ እነዚህን ለመረዳት ይቸገራል፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት በአግባቡ ለአንባቢ እንዳይደርሰው እንቅፋት ፈጠረ ማለት ነው፡፡ በመሆኑም በልቦለድ ውስጥ ጉራማይሌ ቋንቋን አብዝቶ መጠቀም ጉዳት አለው፡፡ ይህን ማለት ግን በፍጹም መጠቀም አይገናም

ማለት አይደለም። ሁሉም አንባቢ ከአውዱ ይረዳል ማለት አይቻልም። ምክኒያቱም የሁሉም አንባቢ ቋንቋእውቀት ደረጃ የተለያየ በመሆኑ ነው።

### 3.3.3. የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ አለመጣጣም

አንድ ደራሲ የተሟላ ሀሳብ የያዘ ሀረግ ብሎ አረፍተ ነገር ለማዋቀር፣ የሚጽፍበት ቋንቋ የአረፍተ ነገር አወቃቀር ስርአት ሂደት ጠንቅቆ ማወቅ ይጠበቅበታል። ባልተስተካከለ የቃላት አቀማመጦችና የድምጾች አሰካክ የአረፍተ ነገር አወቃቀረ ምክኒያት የሚፈጠር ስህተት አንባቢን ግራ ከማጋባቱ በተጨማሪ ሀሳቡን በትክክል ሳይረዳ በደመነፍስ እንዲዘል ያደርገዋል። በደራሲ አቦነህ መድበል ውስጥም በተወሰነ መልኩ የዚህ አይነት የሰዋሰው ስርአቶችን ያፋለሱ ስህተቶች ተፈጽመዋ። ይህን የሚያሳዩ ምሳሌዎች በሚከተለው መልኩ ፈትሻቸዋለሁ። እነዚህንም ሳይ በብዛት የቁጥር የጾታ፣ የእምርነት አለመጣጣሞች/ አለመስተካከሎችን/ ያሳያል።

" እኔ <u>ይወዳል</u>።" /ገጽ፣2/

ይህ የጾታና ማሰሪያ አንቀጽ አለመጣጠም ነው። መሆን ያለበት <u>እወዳለሁ</u>

"እራሷ ቀ<u>ረበ</u>።" /ገጽ፣9/

ይህ የታይፕ ስህተት ካልሆነ የፆታና የማሰሪያ አንቀጽ ችግር አለበት። መሆን ያለበት ግን <u>ቀረበች</u>

<u>"ቅዱስ ማርያም</u>፣ አለሚቱን ከገደልሺልኝ የአስር ሳንቲም እጣን አገባልሻለሁ፡" /ገጽ ፣ 15/

ይህ የጾታ ችግር ይታይበታል። መሆን ያለበት <u>ቅድስት</u>

"እንደዚያ ቀጭን የነበረችው ዕንቡጥ ኮረዳ እንደ ሽቦ በመጠንከሯ ግን <u>አልተቻላቸውም</u>።" /ገጽ፣ 15/

ይህ የጾታ ችግር አለበት። መስተካከል ያለበት <u>አልተቻለቻቸውም</u> ተብሎ ነው።

### 3.3.4 የአረፍተ ነገር ቅንብር ጉድለት

እንደ ሚታወቀው በአማርኛ አረፍረ ነገር ቅንብር ውሰጥ መጀመሪያ ድርጊቱን የሚፈጽመው ባለቤት ይኖራል። ከዚያም ድርጊቱን የሚቀበል ተሳቢ የሚባለው ይኖራል። በመጨረሻም ድርጊቱን የሚገልጽልን ግስ ይኖራል። እነዚህ በቅደም ተከተል ሲቀመጡ ባለቤት + ተሳቢ + ግስ ነው። ይሕ ተለምዷዊ የአማርኛ አረፍተ ነገር

ቅንብር ነው፡፡ አቦነህም ልቦለዱን በሚጽፍበት ጊዜ ከላይ የታየውን የአማርኛውን ተለምዷው የአረፍተ ነገር ቅንብር በአብዛኛው ቢከተልም የተወሰኑ ይህን ህግ ያልተከተሉም አረፍተ ነገሮች አሉ፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን ሀሳብና ተቀነባብሮ የተገኘው አረፍተ ነገር ስሜት የሚይሰጥና ሚያደናግር ከሆነ ነው የአረፍተ ነገር ቅንብር ጉድለት የሚባለው፡፡ በአረፍተ ነገር ቅንብር ሂዳት ላይ እነዚህን ችግሮች ከታዩ አንባቢዎችን ሀሳቡን በቀላሉ ሳይረዱት ያልፉታል፡፡ ሊተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብም ባክኖ ይቅራል፡
ለምሳሌ ያህል ሚከተለውን እንመልከት፡፡

"አዲስ የተገዛውን የክፍለ ሀገር አውቶበብሽስ ብቃትና ጥንካሬ ለመመርመር ጎንደር ሄጀበት ወደ አዲስአበባ ስመለክ ነበር-- በመጀመሪያ ረድፍ ላይ ጂንስ ጃኬት ሱሪ ለብሳ፣ ቦት ቆዳ ጫማ ተጫምታ፣ ብጫሎ ሚስታሸት ያየኋት፡፡" /ገጽ፣13/
በዚህ ረጅም አረፍተ ነገር ውስጥ አንድ ሁኖ የቀረበው አረፍተ ነገር ሦስት ሊሆን የሚገባው ነበር፡፡ ምናልባት ደራሲው ድርጊታዊ ለማድረግ ፈልጎ እንኳ ቢሆን የሥርአተ ነጥብ ጉድለት መታየት አልነበረበትም፡፡ ስለዚህ ሳያጥርም ሆነ ሳይረዝም ይህን ሦስት አረፍተ ነገር ቢሆኑ ይችላሉ ያልኋቸውም፡- "አውቶብሱ አዲስ የተገዛ የክፍለ ሀገር መኪናነው፡፤ ጥንካሬውን ለመመርመር ጎንደር ሄድኩበት፡፡ ወደ አዲስ አበባ ስመለስ በመጀመሪ ረድፍ ላይ ጂንስ ጃኬትና ሱሪ ለብሳ ቦት ጫማ ተጫምታ፣ ብጫ ሎሚ ስታሸት ያየኋት፡፡" "አንችን አያገባሽም እማማ አርፈሽ ተኚ፡፡ ዝምበል፡፡" ቋ፣ቋ፣ቋ፡ ኩርኩምች በተላጭ ራስ ቅል ላይ፡፡" /ገጽ፣14/

በነዚህ አረፍተነገሮች ውስጥ የአረፍተ ነገር ቅንብር ጉድለት ይታያል፡ ፤በአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ያሉ ቃላት መገኘት ባለባቸው ቦታ ባለመገኘታቸው ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት ለአንባቢ ብዙም ግልጽ አይደለም፡፡ እነዚህን አረፍተ ነገሮች የተስተካከለ ለማድረግ ከላይኛው ይልቅ ሚከተለው የተሻለ ይሆናል የሚል ዕምነት አነለኝ፡፡ እሱም፡
"እማማ አርፈሽተኚ ኤገባሽም፡፡ ዝምበል፡፡ ኩርኩም በተላጨ ራስ ቅል ላይ ቋ፣ቋ፣ቋ፣፡፡"
ሌሎችንም ይሻላል ያልኋቸውን ለመጠቆም ያህል፡፡

“መጥረጊያውን ወረወረ። ከጠረጴዛ ሽልኮ ሩጫ። አፈፍ። አለሚቱ የጎንጀባን ሳይሆን የእልኽ የብስጭት ጀሮ እየጎተተች ወደ መኝታ ክፍል አመሩ።” /ገጽ፣13/

“እጀቹን ከአልጋዋ እግር በሲባጎ አቆራኝታ ወደ መስኮቱ ተጠጋች። መልክት፣ ጸጉሯን ነካ--ነካ ቅንድቧን ለሽ --- ለሽ፣ ነጠላዋን አጠፍ ለበስ አድርጋ፣ ጉንጀባን ከተቀመጠበት መሬት ጋር በግልምጫ አጣብቃ ፈትለክ።” /ገጽ፣14/

“ ያኔ ነበር ልመደኛው የቅቤ ቅል መንደር ውሻ አንገቱን ገባ አድርጎ ምላሱን አውጥቶ ሲያለከልክ፣ ሲያፈጥበት ያየው።” /ገጽ፣14/

በአጠቃላ አቦነህ በድርሰቱ ውስጥ ይህን ያህል የጎላ የቋንቋ አጠቃቀም ድክመት አለው ባይባልም ለተለየ አላማ፣ አንባቢያን ወደተለያየ አቅጣጫ እንዲያስቡና ለገጸ ባህሪያህቱ ስብዕና የተለየ አትኩሮት ለመስጠት የቃላት መደገገም ጉራማይሌ ቃላት ፣የባለቤትና ማስሪያ አንቀጽ አለመጣጣምች ተከስተዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ በታይፕ ስህተት የተፈጠሩ መሆናቸውን ተመልክቻለሁ።

# ምዕራፍ አራት

## 4. የልቦለዶቹ ይዘት ትንተና

ስነጽሁፍ የሰዎች የተለያዩ ገጠመኞችና የኑሮ መልኮችን በቋንቋ አማካንኝት ቀልብን በሚስብ መልኩ ተቀናጅቶ የሚቀርብበት ፈጠራዊ ስራ የሆነ አንድ የኪነጥበብ ዘርፍ ነው፡፡ ስነ ጽሁፍ በውስጡ የተለያዩ ዘርፎችን ያቀፈ ሲሆን ከእነዚህም አንዱ አጭር ልቦለድ ነው፡፡

አጭር ልቦለድ እንደሌሎች ስነ ጽሁፍ ዘርፎ ሁሉ በማህበረሰቡ ውስጥ ጎልተው የሚታዩትን ጉዳዮች በማንሳት የሰው ልጅ እለት ተእለት በህይወት ውጣውረድ የሚያጋጥሙትን የህይወት ገጠመኞች ያንጸባርቃሉ፡፡ ከነዚህ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚታዩትን ጉዳቶች በማንሳት ደካማው የሚጎለብትበትን ጠንካራው ይበልት የሚጠነክርበትን እንዲሁም በህብረተሰቡ ውስጥ የሚተዩት ችግሮ እንዲወገድ ያደርጋል፡፡

ይህን ጥናት ሳቀርብ ጥናቱ የተካሄደበት <u>እንቁጤ- ዕንቁጣጣሽ እና ሌሎች ልቦለዶችም</u> የተለያዩ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚታዩትን ጉዳዮች አንስተዋል፡፡ በመድበሉ ውስጥ ካሉ አስር አጫጭር ልቦለዶች ውስጥ ተመርጠው የተተነተኑት ሦስት ብቻ ናቸው፡፡ በልቦለዶቹ የተነሱ ፍሬ ነገሮች የሚከተለውን ይመስላሉ፡፡

### 4.1 እንቁጤ-ዕንቁጣጣሽ

የዚህ አጭር ልቦለድ ታሪክ የተፈጸመው አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሲሆን የሚያነሳው ማህበራዊ ህይወት ነክ ጉዳይ ሲሆን ይህም በአዲስ አመት ወይም ዘመን መለወጫ ላይ

አሉን በብቸኝነት ማሳለፍ ለብአሉ አክባሪዎች ጥሩ አለመሆኑን በዋናው ገጸባህሪይ ሰለሞንና በማዳም አማካኝነት ይግረናል፡፡ ሁለቱ ሰለሞንና ማዳም የአዲስ አመት ብአል ብቻውን እናከብረዋለን ብለው ጭራሹን አለሰብትም ነገር፡፡ ሰለሞን ከንጋት ጋር ሁሌ እንደሚያደረው በዘመን መለጫወ ጭፈራና ዳንስ ቤት ከንጋት ጋር ለማሳለፍ እቅዱ ሁሉ ያለመቻቸው የከዚህ በፊት ህይወቱን ለመገምገም ነበር፡፡ ደራሲው ይህን ሲገልጽ በእንቁጤ-እንቁጣጣሽ ዋዜማ ወትሮ እንደሚያደርገው ከቡና ቤትና ዳንስ ቤት ግርግር ሁካታ፣ ጫጫታ፣ ስካር፣ ቡጢና ፍንከታ ራሱን ለማግለል-- በሌላ በኩል ደግሞ ያለፈው አመት ህይወቱን ለመገምገም የመጪውን አመት ለማቀድ ወረቀት ላይ ቢያሰፍራቸው ካመሸው በርካት ነጥቦች አንዱ ስለንጋት ነበር፡፡” /አቦነህ፡2000፡3/

ሰለሞን ነገሩ ሁሉ ግራ ተጋብቶት ነበር ብአሉን ከጠዋቱ የጀመረው፡፡ የመድፉ ተኩስ፣ የአእዋፋት ዜማ፣ የልጆች ሆያ ሆዬ ጭዋታ፣ የጓደኛሞች ወሬ ወዘተ አልሞት የነበረውን የተዛባ ውሳኔ ላይ ከመድረስ ለመጠንቀቅ ስለ እሷ ማለት ስለ ንጋት በህሊናው የታየውን ሁሉ አስፍሮ ሳይጨርስ ብቸኝቱ እረፍተ ነሳው፡፡ ቤቱ ውስጥ ያሉ እቃዎች ሁሉ ስለ እሱ ብቸኝነት የሚመሰክሩ መሰለው፡፡

“ወለሉ ላይ ደግሞ ቅንብጣቸው የተለቀመላቸው የለዘዙ ቅጠሎች፣ የኮባ ቅጠል፣ የመኪና የውስት አካል፣ የእርሳስ ንድፍ ክላሰር፣ የፔርሙዝ ክዳን፣ ሱሪ፣ ካልሲ፣ ጫማ፣ የአልጋ ልብስ፣ የሥኳር ፍሣሽ፣ የቴፕ ክሮች፣ የሲጋራ ቁራጭ ተበታትነዋል፡፡ ሲያቸው መልሰው ዩታል፡ ፤እንደበታቸውን ሳከፍቱ በልባቸው”አንተ ብቸኛ ሰነፍ” እሉ ሚያፈጡበት መስለው፡ ፤ከአይናቸው ለመሸሸ መብራቱን አጠፉ፡፡ አንሶላውን ተከናንቦ ኩርምት ብሎ ተኛ፡፡” /አቦነህ፡ 2000፣1/

በብአሉ ሰሞን በተለይ በዘመን መለወጫ ልጆች በአበባ አየሁሽ፣ ወጣቶች ከኮረዶች ጋር ሽርሽር የሚያደርጉት፡፡ የቤት ባለቤቶች ከጎረቤት ጋር እየተጠራሩ የእንኳን አደረሳችሁ መልክት መለዋወጥ፡፤ የድግሡ ዝግጅት ማለት ጠላው‹ ዳቦው፣ እንጀራው፣ ስጋው ወዘተ፣ የስጦታ እቃዎች መለዋወጥ የማይቀሩ ነገሮች ናቸው፡፡ ነገር ግን ከእነዚህ ሁሉ ነገሮች የራቁት ማዳምና ሰለሞን ምንም እንኳ በዕድሜ ባይመጣኑም የራሳቸውን ማህበራዊ ህይወት ለማስኬድ ሞክረዋል፡፡

ማዳም በሚያወቁት የመነጋገሪያ ዘዬአቸው ሰለሞንን መልካም አዲስ አመት ካሉ በኋላ የራሳቸው ብቸኝነት እያሳሰባቸው ሰለሞንን እንግዳ ቤትህ የለም ወይ? ኬክ ከቤትና እንብላ ማለቱ ለሰለሞን ብኝነት የተቆረቆሩ ይመስላል፡፡ ሰለሞንም ከፍ ቢል ሰማይ ዝቅ ቢል ምድር ሆነበትና ሁሉ ነገር ወደ ማዳም ያዞረ ይመስል መልካም አዲስ አመት፣ ተሻለዎት እና ምን አለ ወጣት ቢሆኑ ያለው ውስጡ ያለውን የብቸኝነት መንፈስ የተበቀለ መስሎት ነው፡፡

ይሁን እንጅ ሰለሞን ሙሉን የአዲስ አመትን ቀን ብቻው ማሳለፍ አልፈለገም፡፡ ከዚህ በፊት በፍቅር ብዙ ጊዜያትን ያሳለፈቸውን ንጋትን አሰበ፡፡ በሌላ በኩል ንጋትን ቢያስብም በሆነ ነገር ተጋጭተው ስለነበር በተመሳሳይ መልኩ ይህ ነገር ትዝ አለው፡፡ ታዲያ ሰለሞን የአዲስ አመት ብቸኝነት መሮታልና ይቅርታ ለምን አልጠይቃትም ማለቱን አስቧል፡፡

ሰለሞን ንጋትን ይቀርታ ሊጠይቅ ወደ ማዳም ቤት ስልክ ለመደወል እየሮጠ ሲሄድ ያያቸው የነበሩ ጸደይ የመሰሉ ባልና ሚስቶች ኮረዶች በከበሮ ሲደልቁ፣ አበባዎችን፣ የቅዱሳን ስዕሎችን የሚሸጡት ሰዎችንና የሚሳሳሙ ፍቅረኛሞችን ሲያይ ይቅርታ እንዲጠይቅ የባሰ ገፋፋው፡፡ ማዳም ስልክ አስደወሉትና ንጋትን አገኛት፡ ፡ለሶስት ወር ያህል ነበር የተለያዩት ንጋት ምን አመጣህ ብላ ብታስቸግረውም ይቅርታ ልጠይቅ፣ እንኳን አደረስሽ ልልሽ እና እህት ላደርግሽ ብሎ ካሳመነ በኋላ ኡመርካያም ካፌ እንዲናኙ ተቀጣጠሩ፡፡ ሰለሞን የሷን መልስ እስኪሰማ ቋነጠ፡፡ እሺ ስትለው ደስታው ወሰን የለውም፡፡ ጎል እንዳስገባ ኳስ ተጫዋች እየተወረወረ ዘለለ፡፡ ማዳም ኬክና ሻይ በትሪ አድርገው ከጓዳ ብቅ ሲሉም የደሰታው ብዛት አመስግናለሁ ብሎ ወደቀጠሮው ቦታ ሄደ፡፡ ብዙም አልጠበቀ ንጋት ወዲያው መጣችለት፡፡

ሰለሞን የብቸኝነት መንፈስ ተላቀት ወሰን የሌለው ደስታ ይዞት የንጋትን ሰውነቶች መዳበስ ጀመረ፡ ፤ምንም እንኳ በእህትነት ነው ምንቀጥል ብትለውም ከንፈሯን ለመሳምም ወደኋላ አላለም፡ ፤ከገቡበት ሆቴል ያዘዙትን ከተመገቡት በኋላ የሁለታቸውም ፍቅር ጨመረና ይቅርታቸውን አውርደው ከንፈር ለከንፈር መሳሳም

ጀምረዋል፡፡ በፍቅር አዘቅት ተውጠዋል፡፡ የዘመን መለወጫ ወደ ማታ ለሰለሞን መሆኑን አረጋግጧል፡፡ የከረመ ፍቅራቸውን በመሳሳም ከጨረሱ በኋላ ወደ ሰለሞን ቤት አመሩ፡፡

"እንቁጣጣሽ ያን እለት እንደ እንቁጣጣሽ ፈገግ ብላ ዋለች---- በፍቅርና በአንድት ጸሀይ እየፈካች፡፡"/አቦነሀ፡ 2000፡10/

በአጠቃላይ ደራሲው በዚህ ልቦለድ ሊስተላልፍ የፈለገው መልክት በብአላት ወቅት በተለይም በአዲስ አመት ላይ በብቸኝነት መዋል ጥሩ አለመሆኑን በማዳምና በሰለሞን መካከል ያለው ግንኙነት ማህበራዊ ህይወትን እና በተለይ በእንደዚህ ባሉ ወቅቶች ፍቅረኛን ማጣት ጥሩ አለመሆኑን አሳይቷል፡፡

## 4.2 እልከኛው

የዚህ አጭር ልቦለድ ታሪክ የተፈጸመው አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነው፡፡ በልቦለዱ የተነሳው ርእስ ጉዳይ ልጆችን በተለይ የሙት ልጆችን አለመንከባከብ፣ ተገቢ ያልሆነ ስራ ማዘዝ ማንከላቸት፣ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዳይጫወቱ ማደረግ ጥሩ ባለመሆኑና ልሆቹም ተሰቃይተው ካደጉ ባኋላ ጥቱ ጸባይ እንደማይኖራቸው በዋናው ገጸባህሪይ ጎንጀባ አማካንነት እንረዳለን፡፡

የጎንጀባ አክስት አለሚቱ የሚኒስትሪ ተፈታኝ ተማሪ ስትሆን ለጎንጀንባ ያላት አመለካከት በጣም ደካማ ነው፡፡ ለሱ ብቻም ሳይሆን ለእናቱ ያላት ከበሬታ ዝቅተኛ ነው፡፡ ጎንጀባን ባገኘችው ቁጥርለመምታት፣ ለማዘዝ፣ ለማንከላቸት ወደ ኋላ አትልም፡ በዚህ ጊዜ በዕድሜ የገፉ እናቷ ተይ ልጄ የሙት ልጅ አታንከላች ስትላት እንደትናገርና እንድትመክራት አትፈልግም፡፡ ይባስ ብላ አርፈሽ ተኚ፣ አያገባሽም እለች ህገወጥ በሆነ አነጋገር ትገስጻታለች፡፡ በተለይ ደግሞ ሁለት የህጻንና የአሮጌ የአልጋ ቁራኛ አልቀልብም እያለች ምትናገረው ነገር በጎንጀባና በአለሚቱ መካከል ባለው ሁል ጊዜ ረብሻ ለመምከር እንዳይገቡ አስገድዷቸዋል፡፡ ስለሆነም አለሚቱ ወሰን የሌለው እንግልት በጎንጀባ ላይ ማድረስ ሚስጥሯ እንዲወጣባት ሁኗል፡፡ ይህም ኢብራሄም የሚባል የትምህርት ቤት ጓደኛዋ የሰጣትን የፍቅር ደብዳቤ ከደበቀችበት አውትቶ ለአባቷ በማሳየት እንደትቆታ አድርጓታል፡፡ ስለዚህ ለልጆች በጥሩ ነገር፣ ለጥሩ ነገር፣

በጥሩ ሁኔታአሳዳጊና በእንክብካቤ ካላደጉ በስተቀር መጨረሻቸው እነሱም መጥፎ ነገር እንደሚያደርጉ፣ ብዙ ፈተና የሚያደርሱ መሆኑን ያስረዳናል፡፡

ጎንጆባ ከሰፈር ልጆች ጋር እግር ኳስ መጫወትን ይወዳል፡፡ ከልጆቹ መካከልም በጨዋታ ችሎታው፣ በጎል ሙከራው እሱ የተሻለ ሁኖ የቡድኑ አለቃ ነው፡፡ የቡድንናቸው ስም የባለወልድ ሰፈር ቡድን ነው፡፡ ከጃልሜዳሰፈር ቡድን ጋር ሲያደርጉት በነበረው ጭዋታ የመጀመሪያዋን የግብ ሙከራ አድርጓል፡፡ ነገር ግን የአክስቱን መምጣት አለመምጣት ለጎሪጥ እያየ ነበር የሚጫወተው፡፡ “ጎንጆባ፣ የባለወልድ ሰፈር ቡድን ካፒቴን የመጀመሪያውን የጎል ሙከራ አደርጎ ኳሷን ለጥቂት ወደ ውጭ እንዳስወጣ ከሚዳው በታች የጥሪ ድምጽ ተስማ፡፡ በጎን አይኑ ሰረቅ አድርጎ ወደ ቤቱ አየ፡፡ ከሜዳው በታች የጥሪ ነፋስ፣ አንገቷን በመስኮት አውጥታ የምትጣራዋ አለሚቱ መሆኗን ተመለከተ፡፡” /አቦነህ 2000፡11/

ጎንጆባን ከጨዋታው ጆሮውን ይዞ እየጎተተች አስወጣችው፡፡ እምባውን ዱብዱብ እያደረገ ጉንጩን እየነፋ ተከፍቶ ወጣ፡፡ ከወጣ በኋላም የባሰ ግርፊያ ደግሞ ስራ ታዘዘ በታዘዘው ስራም አልተመሰገነም ግን ልቡ ሁሉ ጠቅሎ ያለው ጭዋታው ላይ ነው ምክኒያቱም ጭዋታው ለዋንጫ ነበር ፍልሚያው በሲጋራ ወረቀት የተጠቀለለ ዋንጫ ግን አለሚቱ አልሰደደቸውም፣ አንዱን ሲጨርስ ሌላውን እያደረገች አዘዘችው፡፡ መጨረሻ ላይ ግን አልቻለም ሊገጥማትም ሞክሮ የባሰ ተደበደበ፡፡

አለሚቱ በጎንጆባ ሙከራ የባሰ ተናደደችና ከሱ በላይ የሆነ ስራ ለማሰራትም በኃይል አዘዘቸው ሳይወድ በግድ ጎንጆባን ስራውን ይሰራል፡፡ ምንም እንኳ ተመልሶ ከኳስ ጭዋታ ባይካፈልም የሱ ቡድኖች በማሸነፋቸው ተደስቷል፡፡ ጓደኞቹ ካሸነፉ በኃላ ዋንጫውን ሊሰጡት ቢመጡ እንዳይወጣ ብላ በገመድ አሰረችው፡፡ አያቱን ፍችኝ ቢላትም ከመድከማቸው ተነሳና የአለሚቱን ስድብ ፈርተው ዝም አሉ፡፡ “ጎንጆባ፡፡” የደከመ ድምጽ ከብርድ ልብስ ውስጥ፡፡ “አኩዬ ውሻው በላኝ፡ ፍችኝ፣ ሊበለኝ ነው፡፡ የአያቱ እንባ በጎንና በጎን እየተንከባለለ ወደ አንዱ ጆሮ ወረደ፡፡ “ምን ላድርግ ልጄ፣ ሁለታችንም የአልጋ ቁራኛ፡፡” እንዴት እንፈታታ፡፡ የሁለታችንም ጉሮሮ የአለሚቱ

ጉልበት ምርኮኛ እንዴት እንፈታታ፡፡" የሰለለ ድምጽ ከብርድ ልብስ ውስጥ፡፡" /አቦነህ 2000፡14/

ጎንጀባ ይህ ተመሳሳይ ቅጣት እየበዛበት ሄደ፡፡ እንደ ልቡ ከጓደኞቹ ጋር መጫወት አልቻለም፡፡ ከስራው በተጨማሪ እንክልችቱ በዛበት፡፡ ይህን ከግምት በማስገባት አለሚቱን ከሚኒስተሪ ፈተና እንደትወድቅ፣ ጎልበት አግኝቶ/አድጎ/ እንዲገርፋትና የሩህሩህነት ልቦና እንዲሰጣት ቢሳልም አልደረሰለትም፡፡ በመጨረሻ ምርር ሲለው ነውአንድ ቀን ያየባትን ደብዳቤ ለአባቷ በመናገር ጎንጀባ ጎል ከሚያስገባ ደስታው በላይ ተደሰተ፡፡ እሱ በሚመሰለው ኑሮ መኖር፣ መጫወትና ስራ መስራትም ጀመረ፡፡ አያቱም ምተችበት፣ አለሚቱም በረድ አለች፡፡

### 4.3 ብሩ ብልቢሌ

የዚህ አጭር ልቦለድ ታሪክ የተፈጸመው ሁለት ቦታ ነው፡፡ የመጀመሪያው ጎጃም ውስጥ ከምትገኝ ጣና ዳር አካባቢ ያለች ትንሽ ከተማ ቁንዝላ ውስጥ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነው፡፡ ታሪኩ የሚያጠነጥነው በሁለት ገጸባህሪያች በያይኔ አበባና በቡሩ ብልቢሌ ዙሪያ ነው፡፡ በነዚህ ገጸባህሪያት ምክኒያት የባህልን ምንነትአሳይቷል፡፡ ሁለቱም የዋሽንት ፍቅር ያላቸው በዋሽንት አማካንነት የሚተዳደሩናቸው፡፡ ደራሲው በዚህ ልቦለድ ሊያስተላልፍ የፈለገው ጉዳይ ዋሽንት የደስታ ስሜት የሚፈጥር ለወንድና ለሴት የተሰጠ ጸጋና በዚህም አማካንነት ሕይወትን መምራት እንደሚቻል አሳይቷል፡፡

ያይኔ አበባ አባቷ ከዚህ በፊት ዋሽንት ይችል ነበር፡፡ በዚህ ዋሽንትም ህጻን እያለች ቤተሰቦቿ ያዝናኗት ነበር፡፡ የዚያን ጊዜ ዋሽንትን በውስጧ ፍላጎት እንዲያድረባት ያደረገችው፡፡ "ወተትን ከዋሽንት ዜማ ጋር ተመግባም ያደገችው፡፡ እናት ወተት ከጡሩ ታዋ-በአፍ፣ አባት ዜማ ከሸንበቆው-በጆሮ ባንድነት በመልቀቅ፡፡"/አቦነህ 2000 ፡19/

ያይኔ አበባ ለቤተሰቦቿ ትታዛዝ ነበረች፡፡ በተለይ ለባርካ ዘበኛው አባቷ ቁርስ፣ ምሳ እና እራት በሰአቱ ታቀብለው ነበር፡፡ አባቷም በዋሽንት ሳያዝናና መልሷት አያውቅም፡፡ ግን ይህን ሁሉ ሲደርጉ ሌላ ሰው ማለት የቁንዝላ ህዝብ እንዳይሰማ እየተጠነቀቀ ነው፡፡

ምክንያቱም በነሱ ባህል ዋሽንት የዛር የቆሌ፣ የዕብደትና የስምንተኛው ሺ ምልክት አድርገው የሚወስዱት ያይኔ አበባ ግን ብዙ ጊዜ እየሰማች ዋሽንት ትነፋና ትዝናናበ ነበር። በዚህ የተነሳ የቁንዝላ ህዝብ ይዘባበቱባት፣ ይፈሯትና ይርቋት ነበር።

> ታዲያ ጥቂት የማይባል የቁንዝላ ህዝብ ጉድ አለ። የቡና ረከቦት ቀርቦ እስኪነሳ፣ ከአሀዱ እስከ ሁሩ በሰላም፣ ከዞብል ባርካ መነሻ እስከ መድሻ የሚወጋው ስለ ስንትርትርያው ባለ አውሊያ ሆነ። የዛጎፍ አውሊያ ሰፍሮባታል---- ቡዳ ናት --- ስታድግ ዘማ መሆኗ ነው። ሴት ዋሽንት ከነፋች የስምንተኛው ሺ ምልክት ነው---"ነበር መደምደሚያቸው --- ይህ ነበረ ለጋ አእምሮዋን የሚያመሳቅለው ። /አቦነህ 200 ፡ 19ና 20/

ያይኔ አበባ ቤተሰቦቿ ለዋሽንት መልመድ ትልቅ መስረት ቢሆኗትም በኋላ ግን ከህዝቡ ሀሚት ለመዳን ከስራዋ ለማስቀም ልባቸው አስቧል። በተለይ ግን የአይኔ አበባ እናት ከዋሽንት ለማራቅ ብዙ የማንገራገሪያ ዘዴዎችን ተጠቅማለች።

ይሁን እንጂ ያይኔ አበባ ከዋሽንቷ ያቆማት የለም። የባሰ የሚያበረታተት ሰው አንዱአለም የዞኑ ወባ መከላከያ ሀላፊ አገኘች። አንዱአለም በገንዘብ፣ በምክረና በተለያዩ የስነልቦና ምክሮች እንድትበረታታ አድርጓታል። እሷን በመርዳቱም ከባለቤቱ ጋር እስከመጣላት ደርሷል። ምክያቱም አንዱአለም ሁሌ ከያይኔ አበባ ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት ቅናትና ጥርጣሬ ስላደረባት ነው። ነገር ግን የሱ አላማ ያይኔአበባን ትልቅ ቦታ ማድረስ ነው። ያይኔአበባን አባቷ ከሞተ በኋላም ብዙ ሳትቆይ ከአንዱአለም ጋር አዲስ አበባ በመምጣት በሙዚቃ ትምህርት ቤት በዋሽንት ትመረቃለች። በዚህ የዋሽንት ችሎታዋም ሆቴል ተቀጥራ በማዝናናት ትሰራ ነበር። አንድ ቀን ነበር ከስራ ስትመለስ የብሩ ብልቢሌን ዋሽንት የሰማችው። በዛም ተዋውቀው የዋሽንት ልምዳቸውን የሚለዋወጡት።

ብሩ ማየት የተሳነው የዋሽንት ችሎታው ህዝብን የሚያማልል ነው። ፒያሳ ጊዮርጊስ አካባቢ ካለው አውቶብስ መሳፈሪያ ላይ የሚቆም ሰው ሁሉ የብሩን ጣዕመዜማ ሳይሰማ የሚሄድ ለም። አንዳንድ ቀን ወደ ሌላ ቦታ መሄድ ሲፈልግ ያይኔ አበባ ይዛው ትሄድ

ነገር፡፡ ልብስ፣ ጫማ የሚፈልጋቸውን ነገሮችሁሉ ትገዛለት ነበር፡፡ ከዚህ በኋላም ነበር የሁለቱ ግንኙነት እየጠበቀ የሄደው፡፡ ያይኔ አበባ ከተከራየችበት ቤትም ወስዳ ታሳድረው ነበር፡፡ ይሁን እንጅ ዋሽንት በቁንዝላ አካባቢ ያይኔ አበባ ከመጣችበት ቦታም ሳይሆን አዲስ አበባም እንደ መጥሮ ባህል ስለ ሚቆጠር እንደልባቸው አይነፋም፡፡ አንዴም ሁለቱ በዋሽንት ሲዝናኑ ከጎረቤት ተከልክለዋ፡፡

ይሁን እንጂ የብሩንና የአይኔአበባን ስራ ቀስበቀስ ሌሎችም ለመልመለድ አስበዋል የህብረተሰቡን ባህላዊ አመለካከትም በተወሰነ መልኩ የለወጡት ይመስላል፡፡ ምንም እንኳን  በተለየ መልኩ ሴቶች የያይኔ አበባን እጅ ለማንሳት የውስጣቸውን አውጥተው መተንፈስ ቢያቅታቸውም በዋሽንት ትዳር ፍቅር ውስጥ የገቡት ሁለቱ በዋሽንት የሌሎችን መንፈስ እያደሱ የራሳቸውን ህይወት እየመሩ መኖርን ሽተዋል፡፡ "በአካባቢ የነበረ አንድ ጎረምሳ ዋሽንቱን አቀበለው፡፡ የራሱ ቅኝት አንቆረቆረ- ልብን በሀሴት ሊዳስስ፡፡ የፐላስቲክ ቧንቧ ዋሽንት ይዘው ከፊት ለፊት የተቀመጡት ወጣቶች የጫወታውን ጥበብ ለመቅሰም ጣቶቹ ላየ አፈጠጡ፡፡ ፑ-ሉ-ሉ-...." /አቦነህ 2000፡24/

በአጠቃላይ ደራሲው ከዚህ ታሪክ እንድንረዳ ያደረገን ጉዳይ ዋሽንት የህይወት መምሪያ፣ ለወንድም ለሴትም የተሰጠ ጸጋ፣ በባህል ላይ እንከን የማያመጣ መሆኑን በዋናዋ ገጸባህሪ ያይኔአበባና በብሩ ብልቢሌ አማካንነት ነግሮናል፡፡

# ማጠቃለያ

ስነጹሁፍ ምንጩም ሆነ ግቡ ማህበረሰቡ ነው፡፡ ከተገኘበት ሕብረተሠብ ማህበራዊ መሥተጋብሮች ውጭ ሊሆን አይችልም፡፡ አጭር ልቦለድ ከስነጽሁፍ ዘርፎች አንዱ እንደመሆኑ መጠን ምንም እንኳን ውስብስብ የሆነ የህይወት ገጽታዎች የሚታስተናግድ ባይሆንም ህብተሰቡ ከሚያደርጋቸው ማህበራዊ መስተጋብሮች የአንድን ገጽታ በማንሳት የሰው ልጅ የኑሮ ውጣ ውረድን አጉልቶ የሚያሳይ ቃላቱ ቁጥብ፣ ታሪኩ ያልተንዛዛ፣ አንድ ወይም ሁለት ገጸባሪያት ያሉት ነው፡፡

በ2000 ዓ.ም በእንቁጤ-እንቁጣጣሽ እና ሌሎች ልቦለዶች በተባለው መድብል ውስጥ ከቀረቡት አጠቃላይ አስር አጫጭር ልቦለዶች ውስጥ በዚህ ጥናት ሶስት በዕጣ ተመርጠው ተተንትነዋል፡፡ የተተነተኑትም ከቋንቋ አጠቃቀም አንጻርና ይዘት ነው፡፤ የተተነተኑት ልቦለዶች ይዘታቸው ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ማህበራዊ ግንኙነት እና ባሕላዊ ጉዳዮችን የሚያንጸባርቁ ናቸው፡፡ እነዚህ ልቦለዶች በምን አይነት የቋንቋ አጠቃቀም ማለት የቃላት ምርጫ፣ የዘይቤ አጠቃቀም እንደተጻፉና ያላቸወን የቋንቋ ድክመትም በማንሳት ተተንትነዋል፡፡

ከዚህያም በልቦለዶቹ ይዘት ዙሪያ የመጀመሪያ የተተነተነው አጭር ልቦለድ ላይ ማበራዊ ህወትን በሚያወሳ መልኩ እና በሁለተኛውና በሦስተኛ ደግሞ ባህላዊ ህይወትን በሚያሳይ ሁኔታ ያይኔአበባን ከዋሽንት መከልከልና የአለሚቱ ጎንጀባን ማንከላቸት /ማሰቃየት/ የሚጠቀስ ነው፡፡ ስለዚህ ልጆችን በእንክብካቤ፣ በስርአት ማሳደግ ጥሩ ና የተቀጣ ሁኖ እንዲያድጉ እንደሚረዳ፣ዋሽንት ወንድም ሴትም ሊነፋውና ሲጠቀምበት የሚችል ምንም አይነት ባሕላዊ ችግር ዕንደማያመጣ ከልቦለዶቹ እንረዳለን፡፡

በአጠቃላይ ተመርጠው የተተነተኑት ሶስት ልቦለዶች ቋንቋቸው ለአንባቢ በሚገባ መንገድ፣ ገጸባሪያቱን በሚገልጹና ለአጭር ልቦለድ በሚጻፍበት መልኩ የተጻፉ ቢሆኑም የተወሰኑ ችግሮች እንዳለባቸው አይተን በልበለዶቹ የተነሱ ጉዳዮችን ያየንበት ይህ ጥናት ይህን ይመሥላል፡፡

# ዋቢ መጽሐፍት

ሙሉቀን ታፈሰ፡፡ "በቋንቋዎች ጥናት ተቋም የምረቃ መጽሄት በወጡ አጫጭር ልቦለዶች ላይ የይዘት ትንተና፡፡" የዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1991 ዓ.ም.፡፡

ሜሪ ጃዕፈር፡፡ "ከ1973-1975 ዓ.ም በየካቲት መጽሄት ላይ የወጡ አጫጭር ልቦለዶች ያነሷቸው ማህበራዊ ጉዳዮች፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል ፣ ዲማድ፡ 1975፡፡

ሥሜነህ ባይፈርስ፡፡ "የኃይኢየሱስ ፈቃድ አጭር ልቦለዶች ከአጭር ልቦለድ አላባውያንና የአጻጻፍ ዘዴ አንጻር"፣ ለአርት ባችለር ዲግሪ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1993 ዓ.ም፡፡

ሲሳይ ታደሰ፡፡ "የተስፋዩ ገሠሠ አጭር ልቦለድ ሥራዎች በመተከዥ ውስጥ መገምገም""፣ ለአርት በባችለር ዲግ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡ 1974 ዓ.ም፡፡

ተስፋዬ ጎይቴ፡፡ "በዜና ቱሪዝም የወጡ አጫጭር ልቦለዶች ጭብጦችን መተንተን፡፡" ለአርት በባችለር ዲግ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡ 1979 ዓ.ም፡፡

አቦነህ አሻግሬ፡፡ <u>እንቁጤ-እንቁጣጣሽ እና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች፣</u> አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ ዩቪርስቲ፣ 2000 ዓ.ም

የሻረግ ምትኩ፡፡ "በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የወጡ አጫጭር ልቦለዶችን መገምገም"፣ ለአርት ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡ 1979 ዓ.ም፡፡

ዳግማዊ ኤጌንዶ፡፡ "ሂሳዊ ግምገማ በብርሃን ሸባጥና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች ከአጭር ልቦለድ ዋና ዋና ባህሪያት አንጻር"፣ ለአርት በባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡ 1997 ዓ.ም፡፡

ጌትነት ካሳሁን፡፡ "የአሳመነው ባረጋ የትሮይ ፈረስና ሌሎች አጫችር ታሪኮች"፣ ለአርት በባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡ 1995 ዓ.ም፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ <u>የስነ ጽሁፍ መሰረታውን</u>፡፡ አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ቤቶች፣ 1992 ዓ.ም

___________ <u>የስነ ጽሁፍ መሰረታውን</u>።፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል፣ 1996 ዓ.ም

Bates H.E. <u>The modern short story</u>. Acrtical suwey. Me writers inc. Publishers Boston 16. Massachusetts 1965.

Cuswell, Cheristophor, 1958. <u>Illusion and Reality</u>. NewYork International Publisher.